# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ

## የቴአትር ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ፣ አስተዳደርና አሰራርን ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 4/2004 ለማሻሻልና የኪነ-ጥበብ የፈጠራ ሥራዎች፣የባለሙያዎች የማበረታቻና የአገልግሎት ክፍያ አፈፃፀምን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 94/2014

***መ ግ ቢ ያ***

ቴአትር ቤቶች ካላቸው የሥራ ባህሪይ አንፃር እንደ አትራፊ ድርጅቶች የማይታዩ በመሆኑ ለህብረተሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት በቀጥታ በገንዘብ ሳይተመን በአስተሳሰብ ላይ ለውጥ እያመጡ ህብረተሰቡን በማዝናናት የሚያስተምሩ ዝግጅቶችን በማቅረብ ጤናማና ምርታማ ዜጋ መፍጠር በመሆኑ አደረጃጀቱና አሰራሩም ይህንኑ ዓላማ የተከተለ ሊሆን ስለሚገባ፣

ኪነ-ጥበብን ለልማት ለማዋል ህብረተሰቡን እያዝናኑ በማስተማር ለሚፈጠረው መልካም አስተዳደር ለሚያበረክቱት የፈጠራ አስተዋጽኦና ለሚሰጡት ድጋፍ በየደረጃው የሚያበረታታና ቴአትር ቤቶችን በገበያ ተወዳዳሪ ለማድረግ ውስጣዊ አሰራሩ ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት መሆን ስለሚገባው የውስጥ አሰራር መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፣

የከተማችን ቴአትር ቤቶች የሚታዩባቸውን የአሰራርና የግብአት ችግሮችን በመቅረፍ የህዝቡን ተጠቃሚነት ይበልጥ ለማረጋገጥ የሚስችል የኪነ-ጥበብ ተቋምና የማስፈጸም አመራር አቅም በመፍጠር ሙያዊ ሚናውን በሚገባ እንዲጫወት ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ቢሮው በተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 13 ቢሮው በከተማው አስተዳደር ስር የሚገኙ ቴአትር ቤቶችን እንደሚያስተዳደር፣ እንደሚመራና እንደሚቆጣጠር የተደነገገ ቢሆንም ለቴአትር ቤቶች ተግባርና ኃላፊነታቸውን በግልጽ ያስቀመጠ የውስጥ አሰራር መመሪያ ባለመኖሩ ተግባራት የሚከናወኑት በተለያዩ ኃላፊዎች በሚተላለፉ ደብዳቤዎችና በስብሰባ በሚወሰኑ ቃለ-ጉባኤዎች በመሆኑና ዘመናዊ አደረጃጀት ስላልተፈጠረለት ቢሮው ይህንኑ ችግር ለማስወገድ የቴአትር ቤቶችን አስተዳደርና አመራር ዘመናዊ አደረጃጀት እንዲከተል ማድረግ ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ

ሆኖ በመገኘቱ፣ ይህንን መመሪያ ለማዘጋጀት ጥናት ሲደረግ በቴአትር ቤቶች ከሚታዩት ችግሮች መካከል እንደ መነሻ የተወሰድት ችግሮች ከተውኔት ርክክብ እና አዘጋጅ አመዳደብ ጀምሮ ሰፊ ክፍተት መታየቱ ሲሆን የቴአትር ዝግጅት በመዝገብ በኩል ገቢ መደረግ ሲገባው በቀጥታ ለኪነ-ጥበብ ልማት አመራር ዳይሬክተር እየተሰጠ በኪነ-ጥበብ ልማት አመራር ዳይሬክተር በሚመደብ አዘጋጅ አማካይነት ይሰራ ስለነበረ በጓደኝነት፣ በጥቅምና በመቀራረብ መሠራቱ ደራሲያንን እያስመረረ ለድርሰት እጥረትም እንደ ምክንያት ሆኖ ስለነበረ ይህንን ችግር ለማስወገድ የቴአትር ቤቶች የአገልግሎት አሠጣጥ፣ አስተዳደርና አሜራርን ለመወሰን የወጣው መሜሪያ ቁጥር 4/2004 ፀድቆ ከሰኔ 12/2004 ዓ.ም. ጀምሮ በስራ ላይ እንዲወል ተደርጎ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ መሜሪያው የተለያዩ ክፍተቶች የታየበት መሆኑ ከተለያዩ አካላት ሀሳብ የቀረበ በመሆኑና በሌላ በኩል ደግሞ የኪነ-ጥበብ የፈጠራ ስራዎችንና ባለሞያዎችን ለማበረታታት የሚያስችል የኪነጥብብ የፈጠራ ሥራዎች የባለሙያዎች ማበረታቻና የአገልግሎት ክፍያ አፈፃፀም ደንብ ዝርዝር ጥናት በማስጠናት የሚመለከታቸው አካላት አስተያየት ከሰጡበት በኋላ የአፈፃፀሙም ደንብ ጥር 15 ቀን 2005 በካቢኔ ፀድቆ ቁጥር 53/2005 ተመዝግቦ ታትሟል፡፡ በመሆኑም ቴአትር ቤቶች የሚታይባቸውን ከፍተኛ የአመራርና የአሰራር ጉድለትና ክፍተቶችን ለመሙላት ቀደም ሲል ፀድቆ የነበረውን መመሪያ ቁ 4/2004ን በማሻሻል በከተማው አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 9/2 እና ደንብ ቁጥር 53/2005 አንቀፅ 15 ለቢሮ ኃላፊ በተሰጠው መመሪያ የማውጣት ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## 1. አውጭው መ/ቤት፣

የባህልና ቱሪዝም ቢሮ በአዋጅ ቁ 35/2004 አንቀጽ 46 በተሰጠው ሥልጣንና በአዲስ አበባ አስተዳደር የኪነ-ጥበብ የፈጠራ ሥራዎች፣ የባለሙያዎች ማበረታቻና የአገልግሎት ክፍያ አፈፃፀም ደንብ ቁጥር 53 /2005 አንቀፅ 15 መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ፣

ይህ መመሪያ "የቴአትር ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ፣ አስተዳደርና አሰራን ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 4/2004 ለማሻሻል እና የኪነ-ጥበብ ፈጠራ ሥራዎች፣ የባለሙያዎች ማበረታቻና የአገልግሎት ክፍያ አፈፃፀም ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 94/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን፣

ይህ መመሪያ ቢሮው በአዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 13 በከተማው አስተዳደር ስር የሚገኙ ቴአትር ቤቶችን እንዲያስተዳድር፣ እንዲመራና እንዲቆጣጠር ለቢሮው በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በስሩ በሚተዳደሩ ቴአትር ቤቶችና ከቴአትር ቤቶች አገልግሎት በሚጠይቁት አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. ስለፆታ አገላለጽ፣

በግልጽ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## 5. ዓላማ

1. ኪነጥበባዊ የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ ኪነጥበብ ለልማት በሚል ፍልስፍና የተመሩ፣ የከተማዋን አስተዳደር ቁልፍ የትኩረት አቅጣጫዎች በዋናነት መሠረት ያደረጉ፣ ህብረተሰቡን አያዝናኑ የሚያስተምሩ ልዩ ልዩ የኪነጥበብ ውጤቶችን፣ በተለያዩ የማስተላለፊያ መንገዶች ለህብረተሰቡ በማቅረብ ግንዛቤ በሚያስጨብጡ

ሥራዎች ህዝባዊ ንቅናቄ በመፍጠር በኪነጥበብ ውጤቶቹ የረካ፣ አስተሳሰቡ የተለወጠና ለልማት የተነሣሣ ህብረተሰብ ለመፍጠር፣

2. በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ የሀገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦች ባህል የሚያንፀባርቁ ባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃዎችንና ውዝዋዜዎችን በእኩልነትና በስፋት አዘጋጅቶ በማቅረብ በማንነታቸው እንዲኮሩና በመፈቃቀድ ላይ የመሰረቱትን አንድነት እንዲያጠናክሩ ለማገዝ፣
3. የባህል ወረርሺኞችን በመከላከል በጐ ባህላችንን ለማዳበር በልዩ ልዩ መድረኮችና የኪነጥበብ ውጤቶች በህብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ለመስራት፣
4. የተለያዩ የኪነጥበብ ውጤቶች የፈጠራ ባለቤቶችን፣ የኪነጥበብና የቴክኒክ ባለሙያዎችን እንዲሁም ድጋፍ ሰጪዎችን ለተዋጡ ፈጠራዎችና ሥራዎች የሚያነሣሣና የሚያበረታታ መንፈስ ለመፍጠር፣
5. በግሉ ዘርፍ በከተማዋ እየተስፋፋ የመጣውን አበረታች የሀገርኛ ፊልሞች የማምረት እንቅስቃሴ መስመር እንዳይስት፣ እንደመንግስት ተቋም ኃላፊነቱን ለመውሰድና የወደፊቱን የፊልም እንዲስትሪ እድገት ሀገራዊ ፋይዳ ያለው አቅጣጫ የማስያዝ የአርአያነት ሚና ለመጫወት፣
6. ቴአትር ቤቶች ቀድሞ በተወሰነ መልኩ በመድረክ ብቻ ተወስነው ሲሰጡ የነበረውን አገልግሎት በማስፋት በፊልም፤በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ድራማዎችም አገልግሎቶቻቸውን በማስፋት በገበያ ተወዳዳሪና የልማቱ አጋዥ ኃይል ለማድረግ፣ ለተለያዩ የኪነጥበብ ውጤቶች የፈጠራ ባለቤቶች ውስን የነበረውን አሠራር በሌሎችም አማራጮች በማስፋት የፈጠራ ስራዎች እጥረትን መቅረፍ፣

## ክፍል ሁለት

## 6. ስለ ፕሮሰስ ካውንስል አባላት ፣ ስለ ኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ፣ ስለ ስቴጅ ማናጀርና ስለ ኪነ-ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር ተግባርና ኃላፊነት፣

### 6.1. ስለ ኘሮሰስ ካውንስል አባላትና ተግባርና ሀላፊነት፣

በቢሮው ስር የሚተዳደሩት ቴአትር ቤቶች በBPR ጥናት መሠረት ሁሉም እንደ አንድ ኬዝ ቲም ተቆጥረው ቢጠኑም ካላቸው ልዩ የሥራ ባህሪይ አንፃር እንደ ተቋም ተወስደው በኪነ-ጥበብ ልማት አመራር ዳይሬክተርና በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ተዋቅረው ተግባራቸውን እንዲያከናወኑ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም እስካሁን ከታየው ተሞክሮ ቴአትር ቤቶቹ ራሳቸውን ችለው የግልና የጋራ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ኃላፊነት መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ለቴአትር ቤቶች ከተመደበላቸው የኪነ-ጥበብ ልማት አመራር ዳይሬክተር በተጨማሪ ሥራቸውን በጋራ ኃላፊነት ለማከናውን እንዲችሉ የፕሮሰስ ካውንስል አባላትን (የስራ ዘርፍ ኃላፊዎችን)መሰየምና በግልጽ ማስቀመጥ፣ ተግባርና ኃላፊነታቸውንም መወሰን አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የኘሮሰስ ካውንስል አባላት፡-

1. የቴአትር ቤት የኪነ-ጥበብ ልማት አመራር ዳይሬክተር የፕሮሰስ ካውንስሉ ሰብሳቢ፡፡
2. ስቴጅ ማናጀር
3. ከየዘርፉ የተውጣጡ የኪነ-ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰሮች ((ከቴአትር፣ ከባህላዊ ሙዚቃና ከዘመናዊ ሙዚቃ የተውጣጣ) ሆኖ በቁጥር 5 (አምስት)
4. የሰው ኃይል አስተዳደር ኦፊሰር
5. የግዢና ንብረት አስተዳደር ኦፊሰር
6. የፋይናንስ ኦፊሰር ናቸው

### 6.2. የፕሮሰስ ካውንስል ተግባርና ኃላፊነት፣

1. የቴአትር ቤቱን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ የኪነ-ጥበብ ፈጠራ ውጤቶች የሚዘጋጁበትን

ዕቅድ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያውላል፣ ዕቅድና የሥራ አፈፃፀም ሪፖርትን ይገመግማል፡፡

2. የልማታዊ የኪነ-ጥበብ ውጤቶች ግብአት፣ አቅርቦትና አገልግሎት የሚሻሻልበትን ሁኔታ ተጠንቶ ሲቀርብለት የድርጊት አፈፃፀም ዝክረ ተግባር /TOR/ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
3. የከተማውን ነዋሪ ህዝብ እያዝናኑ በማስተማር የልማታዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ ለማስፈን የሚያስችሉ ጥናቶች በቢሮው ተጠንተው ሲቀርቡለት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
4. ጥራቱን የጠበቀ የባህልና የኪነ-ጥበብ ልማት አገልግሎት እንዲስፋፋ በቢሮው ጥናት ተጠንቶ ሲቀርብለት ዝክረ-ተግባር /TOR/አውጥቶ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
5. ህብረተሰቡን ለሰላም፣ ለዲሞክራሲና ለልማት የሚያነሳሱና ኪነ-ጥበባዊ ብቃት ያላቸው ተውኔቶችና ሙዚቃዎች ተዘጋጅተው አመቺ በሆኑ በመድረክና የመዝናኛ መገናኛዎች እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡
6. ከሚቀርቡት የቴአትርና የሙዚቃ ትርዒቶች እና ከሌሎች አገልግሎቶች የሚገኝ ገቢን እንዲሰበሰብ ያደርጋል፣
7. ለሙያውና ለባለሙያው ዕድገት የሚረዱ ዳሰሳዊ ጥናቶችን እያስጠና የውሳኔ ሀሳብ ለቢሮው ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፡፡
8. የኪነ-ጥበቡን ዕድገት ለማሻሻል የሚረዱና ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመቅረፍ፣ የሥራ ባህልን ለማዳበር፣ የባህል ወረራን ለመከላከልና ልማታዊ ባህልን ለማበልፀግ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፡፡
9. በቴአትር የጽሑፍ ተውኔት መረጣና አዘጋጅ ምደባ ላይ እንዲሁም የቴአትር አቅርቦት (ፕሮዳክሽን) የግምገማ ውጤት የውሳኔ ሀሳብ አግባብ ካለው አካል ሲቀርብለት ያፀድቃል ፡፡ከአቅራቢዎቹ ቅሬታ ከቀረበ ፅሁፈ ተውኔቱንም ሆነ ፕሮዳክሽኑን ተመልክቶ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም የውሳኔ ሀሳቡን የማሻሻልና የመቀየር ውሳኔ ይሰጣል ፡፡
10. ከመንግሥት የልማት ፍላጐትና የለውጥ ፍጥነት ጋር የሚሄድ ወይም የሚመጣጠን የኪነ-ጥበብ የሥራ ውጤቶች የሚመረቱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ በሥራ ላይ ያውላል፡፡
11. ቴአትር ቤቶች ከተቋቋሙበት ዓላማና ተግባር አንፃር በኪነ-ጥበባት ዘርፍ የተሰማሩ ሙያተኞችና የሙያ አመራሮችን አቅም ለማሳደግ የሚያስችል የሙያ ስልጠና የሚገኝበትንና የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ያስፈጽማል፡፡

12. ቴአትር ቤቶች በኪነ-ጥበብ ምርት ውጤቶች ብቁና ተወዳዳሪ ሆነው እንዲገኙ የገበያ ጥናት እንዲደረግ ሁኔታዎች የመቻቻል፡፡
13. የኪነ-ጥበብ ውጤቶች በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ የሚያቀርቡትን ፕሮግራም በማዘጋጀት ሥራዎቹ እንዲተዋወቁ የፕሮሞሽን ሥራ እንዲሰራ ያደርጋል፡፡
14. ለቴአትር ቤቱ የሥራ እንቅስቃሴ ቅልጥፍናና ስኬት አስፈላጊ የሆኑ ንዑሳን ኮሚቴዎችንና ቡድኖችን ይሰይማል፣ ተግባርና ኃላፊነታቸውንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
15. በየጊዜው ከከተማ አስተዳደሩና ከቢሮው የሚወጡትን መመሪያዎችና ዕቅዶችን በመቀበል ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
16. በቴአትር ቤቱ የተሰሩም ሆነ ወደፊት የሚሰሩ የኪነ-ጥበብ ሥራዎች በተለያዩ መንገዶች ተደራጅተው እንዲቀመጡ ያደርጋል፡፡
17. በቴአትር ቤቱ የኪነ-ጥበባት ሂስ የሚደረግበትን ሁኔታ ያመቻቻል ያስፈጽማል፡፡
18. የቴአትር ቤቱ አመታዊ በጀትና የስራ ፕሮግራም በሚመለከታቸው አካላት ተዘጋጅቶ በዳይሬክተሩ ሲቀርብለት ተወያይቶ ያፀድቃል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ያሻሽላል ፡፡
19. የቴአትር ቤቱን ገቢም ይሁን ወጪ አግባብ ካለው አካል ሪፖርት ሲቀርብለት ከፋይናንስ ደንብና መመሪያ አኳያ በትክክል ስለመከናወኑ ይገመግማል የውሳኔ ሃሳቡንም ለዳይሬክተሩ ያቀርባል፡፡

## 6.3. የኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ተግባርና ኃላፊነት፣

የኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለቢሮው የባህል ዘርፍ ም/ቢሮ ኃላፊ ሆኖ የቴአትር ቤቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን አጠቃላይ የቴአትር ቤቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፡፡ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል፡-

1. የቴአትር ቤቱን አመታዊ በጀትና የሥራ ኘሮግራም ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት ለፕሮሰስ ካውንስሉ ያቀርባል፣ በውይይት ዳብሮ የፀደቀውን ተመልክቶ ለቢሮው ያቀርባል፡፡ ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያውላል፡፡
2. የቴአትር ቤቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርቶችን ተዘጋጅተው ሲቀርቡለት ከፕሮሰስ ካውንስል አባላት ጋር ተወያይቶ በየወሩና በየሩብ ዓመቱ ለቢሮው ያቀርባል፡፡

3. በዚህ መመሪያ ከቴያትር ቤቶች አገልግሎት እንዲያገኙ ከተጠቀሱ 3ኛ ወገኖች ጋር የሚደረገውን ውል ቴአትር ቤቱን ወክሎ ይፈርማል፡፡ ሆኖም ከዚህ መመሪያ ውጪ ካሉ 3ተኛ ወገኖች የሚደረጉ ውሎች ሲያጋጥሙ ለቢሮው ያሳውቃል፡፡ ሲፈቀድም ይፈራረማል፡፡በውል አፈጻጸሙም ለሚፈጠሩ ጎድለቶችና ጥፋቶች ተጠያቂ ይሆናል ፡፡
4. በሥራ ላይ የዲሲፒሊን ግድፈት በሚፈጽሙ ሠራተኞች ላይ የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ደንብን ተከትሎ የቀላል ቅጣት እርምጃ ይወስዳል፡፡ ከባድ ጥፋት ተፈጽሞ ሲገኝ ጉዳዩ በዲሲፒሊን ኮሚቴ እንዲታይ ለሰው ኃይል አስተዳደር ይመራል፡፡የዲሲፒሊን ኮሚቴ የውሳኔ ሃሳብ ሲቀርብለት ከቢሮው በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት ይወስናል፡፤ በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 6/2000 አንቀጽ 68 ንዑስ ቁጥር 1 ፊደል ሠ እና ረ ከቀረበለት የውሣኔ ሃሳብ ጋር የራሱን የውሣኔ ሀሳብ ጨምሮ ለቢሮው ያቀርባል፡፡
5. ለቴአትር ቤቱ በተፈቀደው በጀት እና ዕቅድ መሠረት የፋይናንስ ህጐችን ተከትሎ የባንክ ሂሣብ ያንቀሳቅሳል በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት ወጭ ያፀድቃል፡፡
6. የፕሮሰስ ካውንስሉን ውሳኔዎች ተከታትሎ ያስፈጽማል፣
7. የቴአትር ቤቱን ሥራ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ አስፈላጊም ሆኖ ሲገየኘው በዚህ መመሪያ የተሠጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት በውክልና ማስተላልፍ ይችላል፡፡
8. በተጨማሪም ከቢሮው የሚሰጡትን ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ተግባር ያከናውናል፡፡

## 6.4 የስቴጅ ማናጀር ተግባርና ኃላፊነት

የስቴጅ ማናጀር ተጠሪነቱ ለኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ሆኖ የቴአትር ቤቱን የመድረክ እንቅስቃሴ ስራዎችን ይመራል፡፡ ይቆጣጠራል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

1. የቴአትር ቤቱን የልምምድ እና የትርኢት ፕሮግራሞች በማውጣት ለስራ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር አቅጣጫ ያስይዛል፡፡ አንድ የኪነ-ጥበብ ውጤት በሚዘጋጅበት ወቅት የኘሮዳክሹኑን ሂደት በማቀናጀት ይመራል፡፡
2. ለኘሮዳክሹኑ የሚያስፈልጉ ቴክኒካል ግብአቶች በማደራጀት ይቆጣጠራል፡፡

3. የእያንዳንዱን ኪነ-ጥበባዊ ፕሮዳክሽን ዝግጅት ከጀምሩ እስከ ፍፃሜ የተደረጉትን የፕሮዳክሽኑን ሂደት የሚያሣዩ ዶክመንቶች ከሁሉም አቅጣጫ እንዲያዙ ያደርጋል፡፡
4. በእያንዳንዱ ፕሮዳክሽን ሂደት የሙያው ዲሲፕሊን ዘለቄታዊነት ባለው መልኩ እንዲጠበቅ አስፈላጊውን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
5. በቅድመ ፕሮዳክሽን የዝግጅት ወቅት የእያንዳንዱን ፕሮዳክሽን ስክሪፕት ፅሑፍ በሚገባ አንብቦ ዳይሬክተሩ የሚጠይቃቸውን ጥያቄዎች ከእስክሪፕተቱ ጋር በማገናዘብ እንዲሟሉለት ያደርጋል፡፡
6. ለኦዲሽን የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡ እንዲሁም በኦዲሽን ወቅት ዳይሬክተሩ/አዘጋጁ/ የሚፈልጋቸውን ድጋፎች በሙሉ መስጠት፡፡
7. ዳይሬክተሩ ከቡድኑ ጋር በሚያደረገው የመጀመሪያ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ በፕሮዳክሽኑ መነሻ እቅድ ላይ በመወያየት የዳይሬክተሩን/አዘጋጁን/ ፍላጐት ግንዛቤ ይወስዳል ፡፡
8. ከቴአትር ቤቱ እቅድና ከዳይሬክተሩ/አዘጋጁ/ አካሂድ /ፍላጐት/ ጋር በማጣጣም የልምምድና የቴክኒካል ግብአቶች ዝግጅት ሂደት የጊዜ ሠሌዳ ያዘጋጃል፡፡
9. በፕሮዳክሽኑ የዝግጅት ሂደት ፕሮግራምና የጊዜ ሠሌዳ መሠረት የልምምድ ቦታና ለልምምድ የሚያስፈልጉ ቁሣቁሶች እንዲሟሉ ለሚመለከታቸው ያሳውቃል፡፡
10. በልምምድ ወቅት በዳይሬክተሩ/አዘጋጁ/ ፅሑፍ ተውኔቱ ላይ የሚደረጉ ለውጦች በሙሉ በየጊዜው ተዘግበው እንዲያዙ ደርጋል፡፡
11. በልምምድ ወቅት የተደረጉ ለውጦች ተግባራዊ እንዲሆኑ በዳይሬክተሩ/አዘጋጁ/ ውሣኔ እንዳገኙ የሚመለከታቸው ቴክኒካል ባለሙያዎች ጭምር በወቅቱ እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡
12. ፕሮዳክሽኑ በተያዘለት ፕሮግራም መሠረት እየተካሄደ መሆኑን ይከታተላል፡፡
13. በፕሮዳክሽኑ ሂደት ከዳይሬክተሩ/አዘጋጁ/ ጋር እየተገናኙ ኃሳብ በመለዋወጥ የፕሮዳክሽኑን ስኬት ያፋጥናል፡፡
14. በፕሮዳክሽኑ ሂደት የሚከሰቱ ማናቸውንም ችግሮች ለመፍታት ከአቅም በላይ የሆኑትን ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ያሳውቃል፡፡
15. ከፕሮዳክሽኑ ዳይሬክተር/አዘጋጅ/ ጋር ተገናኝቶ በመወያየት ለፕሮዳክሽኑ የሚያስፈልጉ ቴክኒካል ግብአቶችን በዝርዝር እንዲመዘገብ አድርጎ የሚጎለብትበትን መንገድ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

16.ዋናውን የፕሮዳክሽን የጊዜ ሠሌዳ መሠረት በማድረግ ከዳይሬክተሩ/አዘጋጁ/ ጋር በመወያየት የቴክኒካል ግብአቶች የጊዜ ሠሌዳን የፕሮዳክሽኑን ሂደት በማያስተጓጉል ሁኔታ አጣጥሞ ያዘጋጃል፡፡

17.በአጠቃላይ የፕሮዳክሽኑ ሂደት ኪነ-ጥበባዊ ዝግጅቱንም ሆነ ቴክኒካል ፕሮዳክሽን ዝግጅቱን ሙሉ በሙሉ አካቶ የያዘ ዋናውን የፕሮዳክሽን መፅሐፍ /Master script/ እንዲዘጋጅ ያደርጋል ፡፡

18.የቴክኒካል ልምምዱ ፕሮግራም ከመድረሱ ቢያንስ ከሦስትና ከአራት ቀናት በፊት ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲዘጋጁ ያሳውቃል እንዲሁም ሁሉም ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

19.የግምገማ ፕሮግራም ከመድረሱ ቢያንስ ከሦስትና አራት ቀናት በፊት ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲዘጋጁ ያሳውቃል፡፡

20.ከግምገማው ውጤት በኋላ ለእርምት ማስተካከያ ልምምድ የሚያስፈልገውን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

21.ትርኢቱ ለተመልካች የሚቀርብበት ቀን በማኔጅመንት እንደተወሰነ ለሚመለከታቸው ሁሉ ያሳውቃል፡፡

22.ትርዒቱ ለተመልካች በሚቀርብባቸው ፕሮግራሞች በሙሉ አዳራሹ መድረኩ መድረክ ጀርባው ትኬትና መስተንግዶው መብራት፣ ውሃ እና ሌሎችም ቴክኒካል ጉደዮች በተገቢው ሁኔታ መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣል፡፡

23.ተዋንያንና ቴክኒካል ባለሙያዎች በሰዓታቸው መገኘታቸውንና መዘጋጀታቸውን አረጋግጦ ተመልካቹ ወደ አዳራሹ እንዲገባ ትዕዛዝ ሰጥቶ ትርኢቱን ያስጀምራል፡፡

24.በተጨማሪም ከኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተሩ የሚሠጡት አግባብነት ያላቸውን ያከናውናል፡፡

## 6.5 የኪነ-ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር ተግባርና ሃላፊነት

ተጠሪነቱ ለኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ሆኖ የትወና ጥበብ ኬዝ ቲም፣የባህል ሙዚቃ ኬዝ ቲም፣የዘመናዊ ሙዚቃ ኬዝ ቲምን እና የሕዝብ ግንኙነት ኬዝ ቲም የሚመራ ሆኖ ከዚህ የሚከተለውን ተግባራት ያከናውናል፡፤

1. በተቋሙ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ልዩ ልዩ የኪነጥበብ ውጤቶች በጥናት ተለይተው የመጡ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ተወይይቶ የሚሰሩትን መለየትና መወሰን

2. እንዲሰሩ የታቀዱ የተለዩ ርዕሰ ጉዳዮችና የኪነጥበብ ዘርፎች ለድርሰቶች ማስታወቂያ ያወጣል ሊካተቱ የሚገባቸውን መመዘኛ መስፈርቶች በጋራ ተወያይቶ ይወስናል፡፡
3. ለአዘጋጆች ለሙዚቃና ለውዝዋዜ አቀናባሪዎች ማስታወቂያ ለማውጣት ሊካተቱ የሚገባቸው መመዘኛ መስፈርቶችና ደረጃዎችን ተወያይቶ ይወስናል፡፡
4. የኪነጥበብ ውጤቶች ዝግጅቶችን በመገምገም አስተያየትና ድጋፍ ይሰጣል፡፡
5. በተቋሙም ሆነ በልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎች የሚቀርቡ ትርዒቶችን ፕሮግራም በጋራ ተወያይቶ ይወስናል፡፡
6. ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ለኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ያቀርባል ስፀድቅ በስራ ላይ ያውላል ፡፡
7. ለፓናል ውይይቶች ለባህል፣ ለዘመናዊና ለቴአትር መድረክ ዝግጅቶች ለወርክ ሾፖች ለፌሲቲቫሎችና ለልዩ ልዩ ዝግጅቶች አመራርና አቅጣጫ ያስይዛል፡፡
8. በተቋሙ ተዘጋጅተው ለሚቀርቡ የኪነጥበብ ሥራዎች የሚያስፈልገውን በጀት በጋራ ውይይት ያዘጋጃል፣ በፕሮሰስ ካውንስል ሲፀድቅ በስራ ላይ ያውላል፡፡
9. ተቋሙ አዘጋጅቶ በልዩ ልዩ መድረኮች ሚዲያዎች ለሚያቅርባቸው ልዩ ልዩ የኪነ-ጥበብ ዝግጅቶችና ሥራዎች ፕሮግራም ያወጣል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፡፡
10. በተቋሙ ተዘጋጅቶ የሚቀርበውን መጽሔት ቅርጽና ይዘት በጋራ ተወያይቶ በመወሰን አፈጻጸሙንም ተከታትሎ ያረጋግጣል፡፡
11. የየዕለቱን ልምምድ ይከታተላል የሂደቱንም ሪፖርት ያዘጋጃል፣ በልምምድ ወቅትም ባለሙያዎች በወቅቱ መገኘታቸውን ያረጋግጣል፡፡
12. በመድረክም ሆነ ከመድረክ ውጭ የሚቀርቡ የኪነጥበብ ሥራዎች ፕሮግራም ያወጣል ሞያዊ ሥራዎችን ይቆጣጠራል፡፡
13. የኪነጥበብ ዝግጅቶች ለሕዝብ ከመቅረቡ በፊት ለባለሙያዎች የውይይትና የሕዝብ መድረክ ያዘጋጃል፡፡
14. የልዩ ልዩ ትርዒቶችን ግብረ መልሶች በመሰብሰብ ጥናት አጠናቆ ያቀርባል፡፡
15. በተጨማሪም ከኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን አግባብነት ያላቸውን ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## 7. ስለ ቴአትር ተውኔትና የሙዚቃ ድርሰት ገምጋሚ ኮሚቴ መቋቋም፣ የግምገማ መስፈርቶች እና የድርሰት አመራረጥ አሰራር ዝርዝር ተግባራት

### 7.1. ስለ ቴአትር ተውኔት ገምጋሚ ኮሚቴ መቋቋም፣ እና የቴአትር ተውኔት አመራረጥ ዝርዝር ተግባራት

የገምጋሚ አባላት፣ ኮሚቴ ተጠሪነት ለቴአትር ቤቱ የኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

7.1.1. የቴአትር ድርሰት እና ዝግጅት ገምጋሚ ኮሚቴ በፕሮሰስ ካውንስሉ በሚመረጥ የቴአትር ባለሙያ የሆነ በዘርፍ ከተመደበ በኪነ-ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር ሰብሳቢነት ሁለት የኪነ-ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰሮች እና በቴአትር ክፍል ባለሙያዎች የሚመረጡ 2 በቴአትር ጥበባት የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ዲፕሎማ ወይም በተለያዩ የቴአትር ዝግጅቶችና ትወናዎች በብቃት ለረጅም ጊዜ የተሳተፉና ብቃታቸው የተመሰከረላቸው የሲ.ኦ.ሲ መመዘኛ ሰርተፍኬት ያላቸው አባላት ተጨምረው 5 ባለሙያዎች ያለበት ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡ ከመካከላቸው አንዱ ፀሐፊ ይሆናል ውሳኔ አሰጣጡም በውይይትና መግባባት ስምምነት ላይ መድረስ ካልተቻለ ግን በድምፅ ብልጫ ይወሰናል ፡፡ የሥራ ዘመናቸው ሁለት አመት ሆኖ በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

7.1.2. ማንኛውም ለቴአትር ቤቱ የሚቀርበው የተውኔት ፅሑፍ በኮምፒውተር ተጽፎ ከ40-100 ገፅ ያለው ሆኖ በ5 ኮፒ ይሆናል፡፡ የተውኔት ጽሑፍ ወደ ቴአትር ቤቱ ሲመጣ የሠራተኛ መረጃና ሪከርድ ኦፊሰር ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ቅፅ መሠረት ተረክቦ በደራሲው ስም ሳይሆን ኮድ ተሰጥቶት መዝግቦ ይረከባል፣ የኮሚቴው ፀሐፊም ከሠራተኛ መረጃና ሪከርድ ኦፊሰር በፊርማ ከተረከበ በኋላ በኮሚቴው ሰብሳቢ አማካይነት ለኮሚቴው ያቀርባል ኮሚቴውም ፕሮግራም ይዞ ድርሰቱን በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ፊደል ተራ ቁጥር “ ሀ ” መሠረት በተረከበ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ድርሰቱን ገምግሞ ያጠናቅቃል፡፡

7.1.3. ድርሰቱ ከተገመገመ በኋላ ቢያልፍም ባያልፍም በቃለ-ጉባኤ ተዘጋጅቶ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለኘሮሰስ ካውንስል ይቀርባል ውይይት ከተደረገበት በኋላ ይወስናል፣ በውሳኔ መሠረት ድርሰቱ ካላለፈ የግምገማው ሪፖርት በሸኚ ደብዳቤ በሠራተኛ መረጃና ሪከርድ ኦፊሰር አማካይነት ለባለመብቱ ይሰጣል፣ ባለመብቱ በውሳኔው ቅሬታ ካለው ውጤቱን በወሰደ በሦስት ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቢሮው ያቀርባል፡፡ የይግባኝ ቅሬታው የቀረበለት ሀላፊ አቤቱታው በደረሰው በ10 የስራ ቀን ውስጥ ውሣኔ ይሰጣል፡፡ የተሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ ባለመብቱ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ከሌለው የግምገማው ሪፖርት በደረሰው በአራተኛ ቀን ለዚህ ተግባር በተዘጋጀው የድርሰት መመለሻ ቅጽ ከሠራተኛ መረጃና ሪከርድ ኦፊሰር ስክሪፕቱን ይረከባል፡፡

7.1.4. ወደ ቴአትር ቤቱ የመጣው ተውኔት የቴአትር ድርሰት ሳይሆን የቴአትር ኘሮዳክሽን ከሆነ ለቴአትር ቤቱ መድረክ የሚመጥን ስለመሆኑ በድርሰት ገምጋሚ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 በፊደል ተራ ቁጥር “ለ” መሠረት በዝርዝር ከታየ በኋላ ቃለ-ጉባኤው ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለኘሮሰስ ካውንስል ስብሰባ ቀርቦ ይወሰናል፡፡ቃለ-ጉባኤው በፕሮሰስ ካውንስሉ ተመርምሮ ፕሮዳክሽኑ ካላለፈ የግምገማው ሪፖርት ለባለ ኘሮዳክሽኑ ይሰጣል ካለፈ ከቴአትር ቤቱ ጋር ውል ተፈርሞ ወደ ስራ ይገባል፡፡

7.1.5. ቴአትሩ ለመድረክ ከበቃ በኋላ ለተመልካች የቀርበው ቴአትር በገምጋሚ ኮሚቴው ታይቶ ያለፈ ስለመሆኑ ቴአትር ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ በመድረክ መታየት ከጀመረ በኋላ ከተገመገመው ውጭ ይዘቱን ሊለውጥ የሚችል ቃለ-ተውኔት ወይም ድርጊት ወይም ገፀ-ባህሪ ከተገኘበት ለፕሮሰስ ካውንስሉ ሪፖርት ቀርቦ ሲወሰን የተገኘው ነገር በህግ የሚያስጠይቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ቴአትሩ ከመድረክ ይወርዳል፡፡

7.1.6. ከቴአትር ቤቱ መደበኛ ኘሮግራም ውጭ በምሽት ቴአትር ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሚታየው ቴአትር በገምጋሚ ኮሚቴ ታይቶ በኘሮሰስ ካውንስል ከፀደቀ በኋላ የሚታይ ሆኖ ሰዓቱም ከጠያቂው አካል ጋር በሚደረግ ውል ስምምነት መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

7.1.7. ከማንኛውም የቴአትር ኘሮዳክሽን በቴአትር ቤቱ ለማሳየት ጥያቄ ሲቀርብ በኮሚቴው ከመገምገሙ በፊት ከቢሮው የቴአትር ፕሮዳክሽን የሙያና የማሳያ ፈቃድ ስለመኖሩ ገምጋሚ ኮሚቴው ያረጋግጣል ፡፡ ሆኖም ግን ቢሮው የማሳያ ፈቃድ ለመስጠት አመቺ ሆኖ በማያገኝበት ጊዜ ለቴአትር ቤቶች ገምጋሚ

ኮሚቴው እንዲገመግም ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡ ገምጋሚ ኮሚቴውም የግምገማውን ውጤት ለቢሮው ይልካል ፡፡

7.1.8. በቴአትር ቤት ተገምግሞ ያላለፈ ፕሮዳክሽን ባለድርሰቱ በትክክል አልታየልኝም ወይም ተገቢው ውጤት አልተሰጠኝም የሚል ቅሬታ ከተሰማው ቅሬታውን የግምገማ ውጤት በደረሰው በ5 (አምስት) ቀን ጊዜ ውስጥ ለቴአትር ቤቱ የኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ማቅረብ ይችላል፡፡ ዳይሬክተሩም የቅሬታ አቤቱታ በደረሰው በ10 (አስር) ቀን ጊዜ ውስጥ ለቅሬታው መልስ መስጠት አለበት፡፡ በውሳኔው ካልተስማማ ውሳኔው በተሰጠው በሦስት ቀናት ውስጥ ለቢሮው ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ ቢሮውም የቅሬታ አቤቱታ በደረሰው በ10 /አስር/ ቀን ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

7.1.9. አንድ ፕሮዳክሽን ከተገመገመ በኃላ ውጤት ለማሳወቅ የሚፈጀው ጊዜ ከ15 የሥራ ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡ የሚገመገመው የተውኔት ድርሰት ከሆነ ድርሰት ለማግኘት የወጣው ማስታወቂያ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ከሰባ አምስት ቀናት አይበልጥም፡፡

7.1.10. የቴአትር ድርሰት ዝግጅት ገምጋሚ ኮሚቴው ድርሰት ወይም ዝግጅት ሲመረጥ ሙያው የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር ቢመጣስ የግል ጥቅምን ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት መሥራታቸው ሲረጋገጥ የስራ ኃላፊ ወይም የሠራተኛ ተጠያቂነትን ለመወሰን በደንብ ቁጥር 48/2004 መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

7.1.11. የገምጋሚ ኮሚቴ አባል በራሱ የፈጠራ ሥራ ሲገመገም በኮሚቴው ስብሰባ ውስጥ አይቀመጥም፡፡ በምትኩ አንድ ባለሙያ ይመደባል፡፡

7.1.12. አንድ የቴአትር ድርሰት ተገምግሞ ካለፈና ለመድረክ ከበቃ ለገምጋሚ ኮሚቴው በደንቡ መሠረት ብር 2000.00 /ሁለት ሽህ ብር / ይከፈላል፡፡

## 7.2. ስለ ሙዚቃ ድርሰት ገምጋሚ ኮሚቴ መቋቋምና የሙዚቃ ድርሰት አመራረጥ ዝርዝር ተግባራት ፤

7.2.1. ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ሆኖ በካውንስሉ የሚመረጡ የሙዚቃ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር ሰብሳቢ የሙዚቃ አስተባባሪ ፀሐፊ፣ የውዝዋዜ ወይም ዳንስ አሰልጣኝ አባል ያሉት ሆኖ ከሙዚቀኞችና ከድምፃዊያን የሚመረጡ አንድ አንድ ተወካዮች ተጨምረው ኮሚቴው በ5

(አምስት) አባላት ይቋቋማል፡፡ የሥራ ዘመናቸው ሁለት ዓመት ሆኖ በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

7.2.2. የሙዚቃ አዳዲስ ፈጠራ ድርሰቶች የሚሰበሰቡት በቴአትር ቤቶች የአዳዲስ ሙዚቃ ዝግጅት ዕቅድ መሠረት ሆኖ ድርሰቶች ቴአትር ቤቶች ሊዘጋጁ በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ያተኮሩ ሊሆን ይገባል፡፡

7.2.3. የአዳዲስ የሙዚቃ ድርሰቶች ለደራሲያን ጥሪ የሚተላለፈው በቴአትር ቤቶቹ የዝግጅት ዕቅድ መሠረት ዝግጅቱ ከመጀመሩ 30 ቀን አስቀድሞ ማስታወቂያ በማውጣት የሚመረጡትን የፈጠራ ሥራዎች በቴአትር ቤቱ የሠራተኛ መረጃና ሪኮርድ ኦፊሰር ኮድ እየተሰጣቸው ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ በሚገኘው መመሪያ ቅፅ መሠረት ይሰበሰባሉ፡፡

7.2.4. ወደ ቴአትር ቤቶች የሚቀርቡት አዳዲስ ግጥሞች በኮምፒዩተር የተፃፈ ሆኖ በሦስት ኮፒ፣ ዜማና ቅንብሮቹ ደግሞ በካሴት ወይም በሲዲ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

7.2.5. በማስታወቂያ ጥሪ የሚመጡ የዘመናዊም ሆነ የባህል አዳዲስ የፈጠራ ድርሰቶች የሚቀርቡበት ቋንቋ ከአማርኛ ውጭ ከሆኑ ትርጉማቸው ተያይዞ መቅረብ ይገባዋል፡፡ ሆኖም የቀረበበት የብሔረሰብ ቋንቋና ትርጉሙ የተዛባ ሆኖ ከተገኘ ኃላፊነቱ የድርሰቱ ባለመብት ይሆናል፡፡

7.2.6. የተሰበሰቡት የፈጠራ ሥራዎች ተጠቃለው ይገባሉ ተብለው ከተያዘው እቅድ 30 ቀን በኋላ በሚቀጥሉት 15 ቀናት ገምጋሚ ኮሚቴው የመጡትን የፈጠራ ሥራዎች በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 7.5. መሠረት ገምግሞ ያለፉትንና ያላለፉትን ሥራዎች በቃለ - ጉባኤ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለፕሮሰስ ካውንስሉ ቀርበው ውይይት ከተደረገበት በኋላ ይወሰናል፡፡ በውሳኔው መሠረትም ያላለፉ ድርሰቶች ካሉ ከነመግለጫቸው ለባለ መብቶቹ ይመለሳሉ፡፡ ቅሬታ ያለው ባለመብት ውሣኔው በደረሰው በሶስት ቀን ጊዜ ውስጥ ቅሬታውን ለቢሮው ያቀርባል፡፡ ቢሮው ቅሬታው በደረሰ በ10 የሥራ ቀናት መልሱን ያሳውቃል፡፡ ያለፉትን ደግሞ ለየኬዝ - ቲሞቹ አስተባባሪዎች ተሰጥቶ አቀናባሪዎች ተመድበው ወደ ዝግጅት ይገባሉ፡፡

7.2.7. ለቴአትር ቤት የቀረቡት አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎች ከዚህ በፊት በከፊልም ሆነ በሙሉ ሌላ ቦታ ስለመቅረቡ እና ስላለመቅረቡ በሚዲያ ያልተደመጡ

መሆናቸውን ባለመብቱ ከቴአትር ቤቱ ጋር በሚያደርገው ውል መሠረት ኃላፊነት ይወሰዳል፡፡

7.2.8. ኮሚቴው የድርሰት ግምገማና ዝግጅቶች ተጠናቀው ለመድረክ ከበቁ በኋላ በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 8 በተቀመጠው መሥፈርት መሠረት ደረጃ ይሰጣል፡፡

7.2.9. በአንድ ወቅት የአዳዲስ የፈጠራ ሥራዎች ዝግጅት ልምምዱ ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀኖች ውስጥ ተዘጋጅቶ መጠናቀቅና ትርኢቱ ለህዝብ ከመቅረቡ 15 ቀን በፊት ለፕሮሰስ ካውንስሉ አቅርቦ ከተገመገመ በኋላ ዝግጅቱ ከመቅረቡ 10 ቀን በፊት ለቢሮው አሳውቆ ያስገመግማል፡፡

7.2.10. የአንድ ወቅት የሙዚቃ ዝግጅት ለመድረክ እንደበቃ ለግምጋሚ ኮሚቴው በደንቡ መሠረት ብር 2000.00/ሁለት ሽህ ብር/ ይከፈላል፡፡

## 8. <u>የቴአትር ድርሰት እና ዝግጅት የሚገመገሙባቸው ቴክኒካዊ መሥፈርቶችና የደረጃ አሰጣጥ</u> ፣

### 8.1 የድርሰት መገምገሚያ መስፈርቶች/በዘልማዳዊ የተውኔት መዋቅር ለተፃፉ ተውኔቶች/፣

ጽሑፈ ተውኔቱ በማንኛውም ርዕሰ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ሆኖ የሚከተሉትን ቴክኒካዊና ሌሎች መስፈርቶች የሚያሟላ ሊሆን ይገባል፡፡

1. ጽሑፈ ተውኔቱ የሚከተሉትን አምስት የድራማ አላባውያንን ሊያሟላ ይገባል፡፡
   - ሀ. የሴራ አወቃቀርና ጥንካሬ /plot treatmet/
   - ለ. የገፀ-ባህሪያት አሳሳልና/characterization/
   - ሐ. የጭብጥ ገንቢ መሆን /Theme or subject matter/
   - መ. የቃለ-ተውኔቱ ግልጽ፣ተፈጥሯዊና ተገቢ መሆን /Dialogve/
   - ሠ. የመቼት ተገቢነት/setting clarity/ (ጊዜ፣ቦታና ማህበራዊ እውነታው በሚገባ መገለፁ)እነዚህ አላባውያን ተሟልተውና ተጣጥሞሽ ፈጥረው በተውኔቱ ውስጥ መገለፃቸው ሊረጋገጥ ይገባል
2. ጽሑፈ ተውኔቱ የሚከተሉት ድራማዊ መዋቅሮች፡፡
   - ሀ. የእውቂያ አሰረጫጨት /Exposition/
   - ለ. ትውስብ /complication/
   - ሐ. ጡዘት /climax/

መ. ልቀት /Resolution or Denovement/

ሠ. ድምዳሜ/conclusion/የታዳሚውን ሥነ-ልቦና ቆንጥጠው እንዲይዙ ተደርገው መዋቅራቸው ይረጋገጣል፡፡

3. (በኢ-ዘልማዳዊ የተውኔት መዋቅር ለተፃፉ ተውኔቶች)በንዑስ አንቀፆች 7.1. እና 7.2. የተገለፁት መስፈርቶች ቢኖሩም ተውኔቱ በተለየ አቀራረብ ጥበባዊ ውበቱ ሳይጓደል የቀረበ ከሆነ በልማታዊ ቴአትር መገምገሚያ መስፈርቶች ሊገመገም ይችላል፡፡

ሀ/ ማህበራዊ ችግር ለመፍታት የሚያቀነቅን ጭብጥ መያዝ አለበት፣

ለ/ በጥናትና ምርምር የተሰራ መሆን አለበት፣

ሐ/ አሳታፊ ቅርጽና ይዘት ሊኖረው ይገባል፣

መ/ መዋቅራዊ አፃፃፉ ሥነ-ውበታዊ ርቀት እንዳለው መታየት አለበት፣

ሠ/ ገፀ-ባህሪ ላይ በመመርኮዝ ጥያቄ አቅራቢ ሊሆን ይገባዋል፣

ረ/ ቀላልና ግልጽ አሳታፊ ቃለ-ተውኔት መጠቀም አለበት፣

ሸ/ በቅርፁ ውስጥ ከቃላት ይልቅ ድርጊታዊ ነገሮች መታየት አለባቸው፣

4. ጽሑፉ ተውኔቱ ባልተዘወተረ (ባልተደጋገመ) ዘዴ /style/ የተፃፈ ሊሆን ይገባል፡፡ ይኸውም ተውኔቱ ካሁን በፊት መድረክ ላይ ከቀረቡትና በሀያሲያን ከተነገረላቸው ተውኔቶች የተለየ ሊሆን ይገባል ማለት ነው፡፡

5. ተውኔቱ ሁለንተናዊ ይዘት ያለውና አብዛኛውን ዓይነት ተደራሲ የሚመጥን/Universality/ ሊሆን ይገባል፡፡

6. ተውኔቱ ተደራሲውን ከማዝናናት ባሻገር ትምህርታዊና መነጋገሪያ ርዕስ ጉዳይ ያለው መሆኑ ሊጤን ይገባል /challenge the audience/፡፡

7. ተውኔቱ ተዋንያን ተግተው ባህሪያትን እንዲያገኙ የሚያደርግ ሊሆን ይገባል/challeng the actor/፡፡

8. ጽሑፉ ተውኔቱ በቴክኒኩና በይዘቱ በጥልቀትና ክብደት አዘጋጁን ለፈጠራ የሚያነሳሳ ሊሆን ይገባል /challeng the director/፡፡

9. ተውኔቱ ከቴአትር ቤቱ ተጨባጭ ሁኔታ/የመድረክ ስፋትና ፋሲሊቲ አኳያ ጭምር ሊገመገም ይገባል፡፡ ይኸውም በድርሰቱ ውስጥ የተገለፁት ቴክኒካዊ ማቴሪያሎች ቴአትር ቤቱ ካሉት ማቴሪያሎች ጋር የሚመጣጠን መሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ሆኖ አዘጋጁ ባለው መድረክ እና የመድረክ ምጣኔ ላይ የራሱን የፈጠራ አቅም ተጠቅሞ የሚሰራው ከሆነ መጤን ይገባዋል፡፡

10. ተውኔቱ የህፃናት ተውኔት ከሆነ መሥፈርቱ ከላይ እንደተጠበቁ ሆኖ የህፃናትን ሥነ-ልቦና የሚመጥን፣እያዝናና የሚያስተምራቸው እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡

11. ወጥ ድርሰትና የትርጉም ሥራ በግምገማ ወቅት እኩል ጥበባዊ ብቃት ቢኖራቸው ወጥ ሥራው ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡

12. ማንኛውም ወጥ ድርሰት ርዕሱ በሀገራዊ ቋንቋ የተገለፀ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 8.2 የቴአትር አቅርቦት/ዝግጅት መገምገሚያ መስፈርቶች፣

የቴአትር አቅርቦት ለግምገማ በሚቀርብበት ጊዜ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑ ይረጋገጣል፡፡ በአንቀፅ 7.3.1 ከተራ ቁጥር 1 እስ 12 የተገለፁት መመዘኛዎች እንደተጠበቁ ሆነው

**8.2.1 ከቴአትር ቅርጽና መዋቅር አኳያ፡፡**

ሀ. የሙሉ ጊዜ ተውኔት መሆኑ

ለ. የሴራ አካሂድና ጥንካሬ

ሐ. የገፀ-ባህሪያት አሳሳልና ምጣኔ

መ. የቃለ-ተውኔት ተገቢነትና ምጣኔ

**8.2.2 ከጭብጥ አኳያ፡፡**

ሀ. ሁለንተናዊና አስተማሪ ጭብጥ ያለው መሆኑ

**8.3.3 ከአቅርቦት አኳያ፡፡**

ሀ. ትወናው እያንዳንዱን ባህሪ አጉልቶ ያሳየ እና እያንዳንዱ ተዋናይ የተሰጠውን (የሆነውን) ገፀ-ባህሪ በማገባ ስለመጫወቱ

ለ. የመድረክ አጠቃቀሙ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑ

ሐ. የዝግጅት የፈጠራ አቅም ጐልቶ የሚታይበት መሆኑ

መ. የመድረክ ግብአቶች ማለትም መብራት፣ድምጽ፣ ገጽ-ቅብ የመቼትና የእጅ ቁሳቁሶች በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል

8.3.4 የመብራትና የድምጽ ግብአቶች ተውኔታዊ ድባቡን ከመግለጽ ባሻገር በተዋንያንና በተደራሲያን ላይ ጉዳት የማያስከትሉ መሆናቸውን ማረጋገጠ ያስፈልጋል፡፡

8.3.5 ማንኛውም የቴአትር ድምጽ ግብአት (Sound Effect) ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀ ወይም ከሀገርኛ ሙዚቃዎች (ዘመናዊ፣ባህላዊ) የተወሰደ መሆን ይገባዋል፡፡ ሆኖም ግን በትዕይንት ውስጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የውጭ ሀገር

ባህልን የሚያንፀባርቅ ትይንት ካለ የውጭ ሀገር ሙዚቃን መጠቀም ይቻላል፡፡

8.3.6 የተውኔት ዝግጅት ተገምግሞ እንዲስተካከል አስተያየት ከተሰጠ በኋላ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተሻሽሎ ለ2ኛ ግምገማ መቅረብ አለበት በ2ኛ ግምገማ የተሰጡት አስተያየቶች ተሻሽለው ካልተገኙ ለተጨማሪ ግምገማ አይቀርብም፡፡

# 9. አዳዲስ የሚመጡ የሙዚቃ የፈጠራ ሥራ ድርሰቶች የሚገመገሙባቸው ቴክኒካዊ መስፈርቶችና የደረጃ አሰጣጥ፣

## 9.1 የዘፈን ወይም የመዝሙር ግጥም መገምገሚያ መስፈርቶች፣

የዘፈን ወይም የመዝሙር ግጥም የሚከተሉትን መስፈርቶች ሊያሟላ ይገባል፣

ሀ. ቢያንስ በሁለትና ከሁለት በላይ የተከፋፈሉ አንቀፆች ሊኖሩት ይገባል፡፡

ለ. እያንዳንዱ ስንኝ ተመጣጣኝ ሀረጎች ያሉት ሆኖ ሀረጎቹም በጠበቀ ምት ላይ የተመሠረቱ ሊሆን ይገባል፡፡

ሐ. ስንኞቹም ሆኑ ሀረጎቹ ስሜትን ወይም ዜማን ሳይሰባብሩ ግንዛቤንና የአስተውሎት አድማስን ሊያሰፉ ይገባል፡፡

መ. የሚቀርበው ግጥም ይዞ የተነሳውን ርዕሰ ጉዳይ ተከትሎ የተፃፈና እያዝናና የሚያስተምር ሊሆን ይገባል፡፡

ሠ. ግጥሙ አዲስና ወጥ ሊሆን ይገባል፡፡

## 9.2 የዜማ መገምገሚያ መስፈርት፣

ዜማ የተለያዩ ድምፆች ፒቻቸውን /ቃናቸውን/ በጠበቀ (ከፍታና ዝቅታቸው ተሰናስሎ) የሙዚቃ ፎርም ወይም ቅርጽ ተጠብቆ የሚደመጥ ድምጽ ሆኖ የሚከተሉትን ማሟላት ይገባዋል፡፡

ሀ. በየአንቀፁ የተመደቡትን ስንኞች፣ ሀረግ (ቃና)ተከትሎ ቢያንስ ሦስትና ከዚያ በላይ ሊኖረው ይገባል፡፡

ለ. ዜማው ከዚህ በፊት ከተሰሩና በተለያዩ ሚዲያዎች ከሚደመጡት ጋር ምንም አይነት ተዛምዶ የሌለውና ወጥ ፈጠራ መሆን አለበት፡፡

ሐ. እያንዳንዱ (ሜሎዲ)የድምፆችን ከፍታና ዝቅታ ጠብቆ መሰራት አለበት፡፡

መ. ዜማው የአድማጩን ስሜት የሚስብ መሆን አለበት፡፡

## 9.3 የሙዚቃ ቅንብር መስፈርት፣

አንድ የሙዚቃ ቅንብር የሚከተሉትን ሊያሟላ ይገባል፡፡

ሀ. ዜማውን ተከትሎ ሀርሞኒው ሲቀናበርና ለልዩ ልዩ የሙዚቃ መሣሪያዎች በሚሆን መልኩ ተከፋፍሎ ሲቀናበር፡፡

ለ. ዜማ እና ምቱ ተዋህደው ስሜትን ሊገዙ በሚችል ሁኔታ ተሟልተው ሲገኙ፡፡

ሐ. ሜሎዲ፣ሀርሞኒና ሪትም ግሩፖች ተዋህደው የዜማውን አወጣጥና አወራረድ ውበት ጠብቀው ለአድማጭ ቀለል ባለ መልኩ ጆሮ ግቡ ሆነው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

መ. ወጥ የሆኑና ከሌላ ቅንብር ጋር መመሳሰል የለባቸውም፡፡

## 9.4 የውዝዋዜ ወይም ዳንስ ቅንብር መስፈርት፣

ውዝዋዜ ወይም ዳንስ ድምጽና ምትን ተከትሎ የሚደረግ የአካል እንቅስቃሴ ሆኖ የሚከተሉትን ሊያሟላ ይገባል፡፡

ሀ. እንቅስቃሴው የግጥሙን መልዕክት ገላጭ መሆን አለበት፡፡

ለ. የሚቀርብበትን ብሔር-ብሔረሰብ ባህል የሚወክል፣ ያልተከለሰና ያልተበረዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሐ. የውዝዋዜው አሰላለፍ (ኬሮግራፊ) በየዜማዎቹ አወጣጥና አወራረድ የተከፋፈሉ እንቅስቃሴዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

መ. አዲስና ወጥ ሆኖ ከዚህ በፊት ከተሰሩ ውዝዋዜዎች ጋር የማይመሳሰል ምስል መሆን ይገባዋል ፡፡

## 9.5 የሕፃናትና ወጣቶች ሙዚቃ ሊያሟላቸው የሚገባ መስፈርት፣

ከላይ የተጠቀሱት አዲስ የሚመጡት የፈጠራ ሥራች የመገምገሚ ቴክኒካዊ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ዝግጅቶቹ የሕፃናትን ሥነ-ምግባ የሚመጥን እያዝናና የሚያስተምራቸው እንዲሆን ስፈልጋል፡፡

ሀ. ድርሰቶቹ የሕፃናትን የደስታ ምንጭ የሚፈጥሩ

ለ. ገጠመኞቻቸውን የሚያዳብሩ

ሐ. በራስ የመተማመን ብቃታቸውን የሚያጎለብቱ

መ. የቋንቋ ችሎታቸውን የሚያበለጽጉ

ሠ. ምናባዊ አድማሰቸውን የሚያሰፉ

ረ. ስለማህበረሰባቸውና አካባቢያቸው በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ የሚረዳ

ሰ. ውስጣዊ እና ወጭአዊ አካላቸውን ሙሉ አድርጎ ለትምህርት እና ለስራ ንቁ እና ብቁ ማድግን መሰረታዊ ዓላማው አድርጎ ድርሰቶቹ ሊዘጋጁ ይገባል፡፡

## 10. <u>አዳዲስ የሚመጡ የሙዚቃ ፈጠራ ሥራዎች ደረጃ አሰጣጥ፣</u>

### 10.1 <u>አንደኛ ደረጃ የዘፈን ወይም የመዝሙር ግጥም፣</u>

ሀ. ቢያንስ በሁለትና ከሁለት በላይ የተከፋፈሉ አንቀፆች ሊኖሩት ይገባል፡፡

ለ. እያንዳንዱ ስንኝ ተመጣጣኝ ሀረጎች ያሉት ሆኖ ሀረጎቹም በጠበቀ ምት ላይ የተመሠረቱ ሊሆን ይገባል፡፡

ሐ. ስንኞቹም ሆኑ ሀረጎቹ ስሜትን ወይም ዜማን ሳይሰባብሩ ግንዛቤንና የአስተውሎት አድማስን ሊያሰፉ ይገባል፡፡

መ. የሚቀርበው ግጥም ይዞ የተነሳውን ርዕሰ ጉዳይ ተከትሎ የተፃፈና እያዝናና የሚያስተምር ሊሆን ይገባል፡፡

ሠ. ግጥሙ አዲስና ወጥ ሊሆን ይገባል፡፡

### 10.2 <u>አንደኛ ደረጃ የዘፈን ወይም የመዝሙር ዜማ፣</u>

ሀ. ዜማውን ተከትሎ ሀርሞኒው ሲቀናበርና ለልዩ ልዩ የሙዚቃ መሣሪያዎች በሚሆን መልኩ ተከፋፍሎ ሲቀናበር፡፡

ለ. ዜማ እና ምቱ ተዋህደው ስሜትን ሊገዙ በሚችል ሁኔታ ተሟልተው ሲገኙ፡፡

ሐ. ሜሎዲ፣ሀርሞኒና ሪትም ግሩፖች ተዋህደው የዜማውን አወጣጥና አወራረድ ውበት ጠብቀው ለአድማጭ ቀለል ባለ መልኩ ጆሮ ገቡ ሆነው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

መ. ወጥ የሆኑና ከሌላ ቅንብር ጋር መመሳሰል የለባቸውም፡፡

10.3 <u>አንደኛ ደረጃ የዘፈን /የመዝሙር ቅንብር/</u>

ሀ. ዜማውን ተከትሎ ሀርሞኒው ሲቀናበርና ለልዩ ልዩ የሙዚቃ መሣሪያዎች በሚሆን መልኩ ተከፋፍሎ ሲቀናበር፡፡

ለ. ዜማ እና ምቱ ተዋህደው ስሜትን ሊገዙ በሚችል ሁኔታ ተሟልተው ሲገኙ፡፡

ሐ. ሜሎዲ፣ሀርሞኒና ሪትም ግሩፖች ተዋህደው የዜማውን አወጣጥና አወራረድ ውበት ጠብቀው ለአድማጭ ቀለል ባለ መልኩ ጆሮ ገቡ ሆነው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

መ. ወጥ የሆኑና ከሌላ ቅንብር ጋር መመሳሰል የለባቸውም፡፡

10.4 <u>አንደኛ ደረጃ የዘፈን /መዝሙር / የውዝዋዜ ቅንብር፣</u>

ሀ. እንቅስቃሴው የግጥሙን መልዕክት ገላጭ መሆን አለበት፡፡

ለ. የሚቀርብበትን ብሔር-ብሔረሰብ ባህል የሚወክል፣ ያልተከለሰና ያልተበረዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሐ. የውዝዋዜው አሰላለፍ (ኬሮግራፊ) በየዜማዎቹ አወጣጥና አወራረድ የተከፋፈሉ እንቅስቃሴዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

መ. አዲስና ወጥ ሆኖ ከዚህ በፊት ከተሰሩ ውዝዋዜዎች ጋር የማይመሳሰል ምስል መሆን ይገባዋል ፡፡

10.5 <u>ሁለተኛ ደረጃ የዘፈን ወይም የመዝሙር ግጥም፣</u>

በአንደኛ ደረጃ የዘፈን ወይም የመዝሙር ግጥም ከፊደል ተራ ሀ - መ የተቀመጡት መሥፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ የግጥሙ ጭብጥ ወይም ዋናው ሃሳብ ከዚህ ቀደም ከተሠሩ ግጥሞች ጋር በተወሰነ መልኩ የሚመሳሰል ሲሆን፣

10.6 <u>ሁለተኛ ደረጃ የዘፈን ወይም የመዝሙር ዜማ፣</u>

በአንደኛ ደረጃ የዘፈን ወይም የመዝሙር ዜማ ከተጠቀሱት ውስጥ ፊደል ሐ እና መ የተቀመጡት መሥፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ዜማው በተወሰነ ደረጃ ከዚህ በፊት ከተሠሩ ዜማዎች ጋር መመሳሰል ወይም መቀራረብ ያለው ሲሆን፣

10.7 <u>ሁለተኛ ደረጃ የዘፈን ወይም የመዝሙር ቅንብር፣</u>

በአንደኛ ደረጃ የዘፈን ወይም የመዝሙር ሙዚቃ ቅንብር ከተጠቀሱት ከፊደል ሀ - ሐ የተቀመጡት መሥፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ መግቢያና መሸጋገሪያው ላይ ከዚህ በፊት ከተሠሩ የሙዚቃ ቅንብሮች ጋር በተወሰነ መልኩ መመሳሰል ያለው ሲሆን፣

10.8 ሁለተኛ ደረጃ የዘፈን ወይም የመዝሙር ፡ውዝዋዜ ቅንብር፣

በአንደኛ ደረጃ የዘፈን ወይም የመዝሙር የውዝዋዜ ቅንብር ከተጠቀሱት ከፊደል ሀ - ለ የተቀመጡት መሥፍርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ቅንብሩ በተወሰነ መልኩ ከዚህ በፊት ከተሠሩት ኬሮግራፊዎች ምስል ቅንብር ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን፣

10.9 ሶስተኛ ደረጃ የዘፈን /የመዝሙር / ግጥም፣

ሀ. ግጥሞቹ የህገረሰቡን ቱባ ያገባጠም ዘዴ እና ህብረተሰቡ በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ዘፈኖች ውስጥ በተደጋጋሚ የሚጠቀምባቸው ተለምዶአዊ ግጥም ሆነው በተወሰነ መልኩ ተሻሽለው ሲቀርቡ፡፡

ለ. ግጥሞቹ ከላይ በተጠቀሰው በፊደል ሀ መልክ ሆኖ አቀራረባቸው ወይም ምታቸው መሠረታዊ ይዘታቸውን ሳይቀይሩ በተወሰ መልኩ ተሻሽለው የቀረቡ ሲሆን፣

ሐ. ከላይ በሀ እና በለ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ቢኖሩም የቀረቡበትን ቋንቋ ዘይቤ የማይለውጥ ሲሆን፣

10.10 ሶስተኛ ደረጃ የዘፈን /መዝሙር/ዜማ፣

ሀ. ዜማዎቹ የህገረሰቡን ቱባ ባህላዊ የአዛዚያም ዘዴና ህብረተሰቡ በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ዜማዎች ውስጥ የተጠቀመባቸውን ተለምዶአዊ ዜማዎች ሆነው በተወሰነ መልኩ ተሻሽለው ሲቀርቡ፣

ለ. ዜማዎቹ ከዚህ በላይ በሀ የተጠቀሰው እንደተጠበቀው ሆኖ አቀራረባቸው መሠረታዊ ይዘታቸው ሳይቀይሩ ተሻሽለው የቀረቡ ሲሆን፣

ሐ. በሀ እና በለ የተጠቀሱት ሆኔታዎች ቢኖሩም የቀረቡበትን ማህበረሰብ የአዛዚያም ዘይቤ የማይለውጥ ሊሆን ይገባል፡፡

10.11 ሶስተኛ ደረጃ የዘፈን /የመዝሙር/ ሙዚቃ ቅንብር፣

ሀ. ከዚህ በፊት በተለያዩ ሚዲያ ላይ የቀረቡ የሙዚቃ ቅንብሮችን የተወሰነ ለውጥ አክለውበት ሲቀናበር፣

ለ. ከዚህ በፊት የተቀናበሩ ሙዚቃዎችን እንደየ ኦርኬስትራው ወይም ሙዚቃ ግሩፑ ባህሪይ ለኦርኬስትራው አመቼ እንዲሆን አድርጎ ሲያቀርብ፣

10.12 ሶስተኛ ደረጃ የዘፈን ወይም የመዝሙር ውዝዋዜ ቅንብር፣

ሀ. ውዝዋዜዎቹ የህገረሰቡን ቱባ ባህላዊ የውዝዋዜ ዘዴ እና ህ/ተሰቡ በተለያየ ጊዜ በተለያየ ባህላዊ ውዝዋዜዎች ውስጥ የተጠቀመባቸውን ተለምዶአዊ ውዝዋዜዎችበተወሰነ መልኩ ተሻሽለው ሲቀርቡ፣

ለ. ውዝዋዜዎቹ ከላይ በተጠቀሰው መልክ ሆነው አቀራረባቸውም መሠረታዊ ይዞታቸውን ሳይቀይሩ በተወሰነ መልክ ተሻሽለው ሲቀረቡ፣

ሐ. በሀ እና በለ የተጠቀሱት ሆኔታዎች ቢኖሩም የቀረበበትን ማ/ሰብ ባህላዊ ውዝዋዜ የማይለውጥ ሊሆን ይገባል፡፡

# ክፍል አራት

## 11 ስለ ዳይሬክተር / አዘጋጅ / እና ሙዚቃ አቀናባሪ አመዳደብ፣

### 11.1 ስለ ዳይሬክተር /አዘጋጅ/ አመዳደብ፣

አዘጋጅ ተመርጦ የሚቀርበው በድርሰት ገምጋሚ ኮሚቴ በኩል ሲሆን አመራረጡም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

11.1.1. ድርሰት ከተመረጠና በፕሮሰስ ካውንስል ከፀደቀ በኋላ ቴአትር ቤቱ ገምጋሚ ኮሚቴው የመረጠውን ድርሰት የሚመጥን ባለሙያ በአዘጋጅነት ለመመደብ እንዲያስችለው በቅድሚያ ከቴአትር ቤቱ በተቀመጠው መሥፈረት እንዲወዳደሩ ይጋብዛል ከቴአትር ቤቱ ተወዳዳሪ ካልተገኘ በቢሮው ስር ካሉት ቴአትር ቤቶችና ከቢሮው ባለሙያዎችን ጭምር በማስታወቂያ ይጋብዛል፡፡ ከዚያም ካልተገኘ ከውጭ በግልጽ ማስታወቂያ ይጋብዛል፣ ተወዳዳሪ አዘጋጆች ሲቀርቡም የድርሰቱ ኮፒ ይሰጣቸዋል፡፡

11.1.2. ከቢሮው ወይም ከቴአትር ቤቶች ውጭ የሚጋበዝ አዘጋጅ በዚህ መመሪያ የተገለፀው መመዘኛ እንደተጠበቀ ሆኖ በቴአትር ወይም በፊልም ስራ እንዲሰማራ ከቢሮው ዕውቅና የተሰጠው ሊሆን ይገባል፡፡

11.1.3.የሚወዳደሩት ባለሙያዎች የተመረጠውን ድርሰት በምን መልኩ ሊያዘጋጁት እንደሚፈልጉ የሚያቀርቡትን መግለጫና ሀሳብ /ፕሮፖዛል/ ለመረጃና ሪከርድ ኦፊሰር ሲያቀርቡ ኮሚቴው ከሠራተኛ መረጃና ረከርድ ኦፊሰር ተረክቦ ይገመግማል፡፡

11.1.4. ኮሚቴው ከእያንዳንዱ ተወዳዳሪ የቀረበውን መግለጫና ሀሳብ /ፕሮፖዛል/ ከሚዘጋጀው ተውኔት መለኪያና መመዘኛ አንፃር ገምግሞ የተሻሉትን በመምረጥ ከ3 ያላነሱ ዕጩዎችን ከቴአትር ክፍሉ ሠራተኞች ጋር በአካል አቅርቦ የተዘጋጀበትን ፕሮፖዛል በጥያቄና መልስ አወያይቶ የተሻለ ይመርጣል፡፡ በዚህ አሰራር የተመረጠ አዘጋጅ በፕሮሰስ ካውንስሉ ቀርቦ መፅደቅ አለበት፡፡ይሁን እንጂ ቁጥሩ ከላይ የተገለጸው አዘጋጅ ባይገኝ ድጋሚ ማስታወቂያ ወጥቶ አንድ ሰውም ቢቀርብ በዚህ አንቀፅ 9.1.7. የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ ለፕሮሰስ ካውንስሉ ቀርቦ ይፀድቃል፡፡

11.1.5. የቴአትር ቤቱ የኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተር በቴአትር ክፍሉ የተመረጠውን አዘጋጅ ለፕሮሰስ ካውንስሉ በማቅረብ ካፀደቀ በኋላ ከተመረጠው አዘጋጅ ጋር ውል ይፈርማል፡፡

11.1.6. አዘጋጁም ለቴአትሩ የሚመጥኑ ተዋናዮችን በዚህ መመሪያ በተቀመጡት መመዘኛዎች መሠረት ከመረጠ በኋላ ዝግጅቱን ይቀጥላል፡፡

11.1.7. ለአዘጋጅነት ውድድር የሚቀርቡት (የሚጋበዙት) ባለሙያዎች በቴአትር ጥበብ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ዲፕሎማ ያላቸውና በአዘጋጅነት ወይም በትወና ወይም ሙያውን በማሰልጠን ከ2 ዓመት ያላነሰ ልምድ ያላቸው ይሆናሉ፡፡ ፕሮዳክሽን ከውጭ ተዘጋጅቶ ሲመጣም የቀረበው ቴአትር በገምጋሚ ኮሚቴ ብቃቱ ከተረጋገጠ የአዘጋጁን ተፈላጊ ችሎታዎች ኮሚቴውም ሆነ ቴአትር ቤቱ ማወቅ አይጠበቅበትም፡፡

11.1.8. የዝግጅት ፕሮፖዛሉን በመመርመር አዘጋጅ የሚመረጠው ቢቻል በውይይትና በመግባባት ላይ በመድረስ ይሆናል፡፡ ካልተቻለ ግን በድምፅ ብልጫ ይወሰናል፡፡

11.1.9. አንድን ቴአትር ለማዘጋጀት የሚፈጀው ጊዜ ከሁለት ወር መብለጥ የለበትም፡፡

11.1.10. ከመድረክ የወረደ ቴአትር በድጋሚ ወደ መድረክ መመለስ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የቀድሞው አዘጋጅ በህይወት ከሌለ ወይም ማዘጋጀት የማይችልበት ደረጃ ላይ ካለ በአንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 11.1.7 ላይ በተቀመጠው መሥፈርት መሠረት ሌላ አዘጋጅ ይመረጣል፡፡ በቴአትር ሙያ የተመረቀ ከሆነ ራሱ እንዲያዘጋጀው በቴአትር ጥበብ ያልተመረቀ ከሆነ ወይም አዘጋጁ የሌለ ወይም በወቅቱ ማዘጋጀት የማይችል ከሆነ በዚሁ መመሪያ መሠረት ሌላ አዘጋጅ ተመርጦ እንዲያዘጋጀው ይደረጋል፡፡

## 11.2 የሙዚቃ አቀናባሪ አመዳደብ፣

11.2.1 በገምጋሚ ኮሚቴ ተገምግሞ ያለፉ አዳዲስ ግጥምና ዜማዎች ለሙያው በተመደበው የኪነ -ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር አማካኝነት ኬዝ ቲሙ ተወያይቶ በኬዝ ቲሙ ውስጥ ላሉ አቀናባሪዎች ይሰጥና ወደ ሥራ ይገባሉ፡፡

11.2.2 ከላይ የተገለፀው ሀሣብ እንደተጠበቀ ሆኖ የአንድ ወቅት አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎች ሁሉንም በአንድ አቀናባሪ እንዲቀናበሩ ከተፈለገ፡፡ ድርሰቶች እንዳለፉ ለአቀናባሪዎች ለ15 ቀን የሚቆይ ማስታወቂያ ይወጣል፡፡ በወጣው ማስታወቂያ መሠረት ተወዳዳሪዎቸ የሚከተሉትን ሊያሟሉ ይገባል፡፡

ሀ/ በሙያው ከታወቀ የትምህርት ተቋም ዲግሪና በማቀናበር ስራ 3 ዓመት የስራ ልምድ ያለው ወይም ዲፕሎማ ኖሮት በማቀናበር ስራ 5 አምስት ዓመት የስራ ልምድ ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

ለ/ በሙያው ስራ ከቢሮው የስራና የሙያ ፈቃድ ያለው

ሐ/ በወጣው ማስታወቂያ መሠረት የተመዘገቡ አቀናባሪዎች እያንዳንዱን ድርሰት የሚያቀናብሩበትን ኘሮፖዛል ያቀርባሉ፡፡

መ/ የሙዚቃ ድርሰት ገምጋሚ ኮሚቴው የቀረቡትን ኘሮፖዛሎች በማወዳደር ከ1 -3 የወጡትን አቀናባሪዎች ከዝርዝር መግለጫ ጋር ለኘሮሰስ ካውንስል ያቀርባል፡፡

ሰ/ የኘሮሰስ ካውንስሉ የቀረበለትን ዝርዝር መግለጫ ካየ በኃላ እንዲያቀናብር የተመረጠውን ሙያተኛ ውሣኔ ያፀድቃል፡፡ የኪነ-ጥበብ ዳይሬክተሩም ከአቀናባሪው ጋር ውል ተዋውሎ ወደ ሥራ ይገባል፡፡

## ክፍል አምስት

12 **ስለ ቴአትር የመድረክ ቆይታ ጊዜ፣ ከቴአትር ቤት ውጭ የሚገኙ ተጋባዥ የኪነ-ጥበብ ሙያተኞች ስለሚጋበዙበት አሰራር እና ስለ ኪነ - ጥበብ አገልግሎት ጥያቄ አቀራረብ፣**

12.2 **ከቴአትር ቤት ውጭ የሚገኙ ተጋባዥ የኪነ-ጥበብ ሙያተኞች ስለሚጋበዙበት አሠራር፣**

ቢሮው በሚያስተዳድራቸው ቴአትር ቤቶች ውስጥ የሚገኙት ተዋንያን፣ ሙዚቀኞች፣ ተወዛዋዦችና የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች በBPR ጥናት መሠረት የሥራ መደባቸውና ደረጃቸው ተመሳሳይ ቢሆንም አንድ ባለሙያ ከሌላው ባለሙያ በተለያዩ ምክንያቶች የተሻለ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ ሆኖም እያንዳንዱ ቴአትር ቤት የሚቀጥራቸው ባለሙያዎች ለሥራው ብቃት አላቸው ተብሎ ስለሚቀጠሩ ከተቀጠሩ በኋላ ብቃታቸውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የማብቃትና የማበረታታት ኃላፊነት ያለበት ቴአትር ቤቱ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በመንግስት የሠራተኞች አስተዳደር ህግ መሠረት ለባለሙያዎች ሥራ ሰጥቶ የማሰራት ኃላፊነት ያለበት አሰሪው ስለሆነ በዚህ መርህ መሠረት ማሰራት ግዴታው ነው፡፡ ነገር ግን፣

1. ቴያትር ቤቶቹ ያሏቸው ሙያተኞች ውስን በመሆናቸው ባሉት ሙያተኞች ብቻ ሁል ጊዜ የሚዘጋጁ ዝግጅቶች የተመልካችን ቀልብ ገዝቶ የመያዝ ችግር በመኖሩ፣
2. ወቅትን ተከትለው ከመንግሥት የትኩረት አቅጣጫ ጋር ተቀናጅተው የሚቀርቡት የሙዚቃ ዝግጅቶች አሰልቺ እንዳይሆኑና በየዝግጅቶቹ ጣልቃ የተለያየ ታለንቶች ያላቸው ሙያተኞች እንዲገኙ መደረጉ ተመልካች ዝግጅቶችን በተደጋጋሚ እንዲያያቸው ለማድረግ፣
3. በቴአትር ቤቶች ያሉ ሙያተኞች በየጊዜው የተሻለ ደመወዝና ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ስለሚሄዱ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ደግሞ ተጋባዥ አርቲስቶችን እየጋበዙ ማሠራት ተገቢ በመሆኑ፣ በአጠቃላይ የቴአትር ቤቶች በየጊዜው አሠራራቸውን መለወጥና የተመልካችን ፍላጎት አሟልተው የሚጠበቅባቸውን ድርሻ ለማበርከት ከላይ የተጠቀሱት የአሠራር መርህ መከተል ወቅቱ የሚጠይቅ በመሆኑ እና የሚቀርበው ትርኢት በባህሪው ውስብስብነት ምክንያት ከቴአትር ቤቶች ውጭ ያሉ ባለሙያዎችን መጋበዝ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሚከተለውን አሰራር ተከትሎ መፈፀም አለበት፡፡

12.2.1 የሚዘጋጀው ቴአትር ከሆነ አዘጋጁ ባለሙያዎችን ሲመርጥ /ሲመድብ/ ቴአትር ከሚዘጋጅበት ቴአትር ቤት ወይም በቢሮው ስር ከሚገኙ ቴአትር ቤቶች ገፀ - ባህሪውን የሚሸፍን ባለሙያ ማግኘት ካልተቻለ የቴአትር ክፍሉን ሠራተኞች በማወያየት ከውይይቱ የተገኘውን ሀሣብ ከራሱ ሀሣብ ጋር ጠምሮ በኘሮሰስ ካውንስል በማፀደቅ በውል ሊመደብ ይችላል፡፡

12.2.2 የሚዘጋጀው ሙዚቃ ከሆነ ሙዚቀኛ ወይም ድምፃዊ ለሚዘጋጀው ሥራ የሚመጥን በቴአትር ቤቱ ውስጥ ካልተገኘ የሙዚቃ ክፍሉን ሰራተኞች በማወየያት በውይይቱ የተገኘውን ሀሣብ ከራሱ ሀሣብ ጋር ጠምሮ በቅድሚያ በቢሮው ስር ላሉት ቴአትር ቤት ባለሙያዎች ቅድሚያ በመስጠት በኘሮሰስ ካውንስል በማፅደቅ በውል እንዲጋበዝ ይደረጋል፡፡

12.2.3 ከላይ በቁጥር 12.1.1. እና 12.1.2. በተጠቀሰው መሠረት አሠራሩ እንደተጠበቀ ሆኖ የጥበባቱ የደረጃ መሥፈርት እንደሚተለው ይሆናል፡፡

## 12.3 <u>የተጋባዥ ተዋናይ የችሎታ ደረጃ መመዘኛ መሥፈርት፣</u>

### 12.3.1 <u>የአንደኛ ደረጃ ተጋባዥ ተዋናይ /መሪ ተዋናይ/</u>

**ሀ/** በቴአትር ተመልካች ህ/ተሰብ ዘንድ በተዋናይነት ችሎታው የታወቀ፣

**ለ/** ቀደም ሲል ለተመልካች በቀረቡ ከ5 ባላነሱ ተውኔቶች የመሪ ገፀባህሪ ሚና ተጫው የተወደደ /**የተመሰገነ**/ ወይም በአጭር ግዜ በተለያዩ ሚዲያዎችና ቴአትር በሠራቸው ሥራዎች በሙያው ብቃት ታዋቂነት ያተረፈና በአዘጋጁ ለተመረጠ ገፀ -ባህሪይ ተስማሚሆኖ የተገኘ፣

**ሐ/** ውስብስብ ገፀ - ባህሪያትን መጫወት የሚያስችል የሙያ ችሎታና ብቃት ያለው፣

**መ/** እንዲጫወተው/ እንዲሠራው/ የሚሰጠውን ገፀ - ባህርይ የፈጠራ ችሎታውን በመጨመር ማዳበር የሚችል፡፡

**ሠ/** በልምምድና በትርዒት ወቅቶች ሰዓትን በማክበር በሙያ ሥነ - ምግባሩ ለሌሎች አጋር ባለሙያዎች መልካም አርአያ የሚሆን ተዋናይ መመዘኛውን ማሟላቱ የቴአትር ቤቱ የኪነ -ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ፣ስቴጅ ማናጀር እና የኪነ -ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር አምነው ሲያረጋግጡ እና በኪነ - ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ሲፀድቅ ለዚህ አንደኛ ደረጃ ተጋባዥ ተዋናይ

በዚህ መመሪ ላይ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት ክፍያው ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

12.3.2 **ሁለተኛ ደረጃ ተጋባዥ ተዋናይ፣**

**ሀ/** በቴአትር ተመልካቾች ዘንድ ታዋቂ የሆነ፣

**ለ/** ቀደም ሲል ለተመልካች በቀረቡ ከአምስት ባላነሱ ተውኔቶች ውስጥ በማንኛውም የተሰጠውን የገፀ-ባህርይ ሚና በአግባቡ ተጫውቶ የተመሰገነ፣

**ሐ/** ለተጋበዘበት ተውኔትና ለሚመደብበት ገፀ -ባህርይ አስተማማኝ ችሎታ ያለው፣

**መ/** በልምምድና በትርዒት ወቅቶች ሰዓትን በማክበር በሙያ ሥነ - ምግባሩ ለሌሎች አጋር ባለሙያዎች መልካም አርአያ የሚሆን ተዋናይ መመዘኛውን ማሟላቱ የቴአትር ቤቱ የኪነ -ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ፣ስቴጅ ማናጀር እና የኪነ -ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር አምነው ሲያረጋግጡ እና በኪነ - ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ሲፀድቅ ለዚህ አንደኛ ደረጃ ተጋባዥ ተዋናይ በዚህ መመሪያ ላይ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት ክፍያው ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

12.3.3 **ሶስተኛ ደረጃ ተጋባዥ ተዋናይ፣**

ሀ/ ቴአትር የመጫወት ተሰጥኦና ዝንባሌ ያለው፣

ለ/ ቢቻል በትልልቅ የመድረክ ተውኔቶች ወይም አጫጭር ድራማዎች ላይ ትናንሽ የአጃቢ ገፀ - ባህርያትን የተጫወተ /የተሳተፈ/

ሐ/ በልምምድ ኘሮግራሞችና በትርዒት ወቅቶች ሰዓትን አክብሮ መገኘት የሚችል፣

መ/ ለተውኔት ትርዒቱ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናትና ወጣቶች ሲያስፈልጉና ከላይ የተዘረዘሩት መስፈርቶች ቀደም ሲል በተጠቀሱት የቴአትር ቤቱ ወሳኝ አካላት ሲታመንበት፣ በዚህ መመሪያ ላይ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት ክፍያው ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

12.4 <u>የተጋባዥ የሙዚቃ ጥበብ የችሎታ ደረጃ መመዘኛ  መሥፈርት፣</u>

12.4.1 <u>የአንደኛ ደረጃ ተጋባዥ ድምጻዊ፣</u>

ሀ/ በተመልካች /**አድማጩ**/ ሕብረተሰብ ዘንድ በድምጻዊነት ሙያው የተደነቀ፣ እና ደረጃውን በጠበቀ ባለኮከብ ሆቴል ውስጥ በድምፃዊነት አራት ዓመት የስራ ልምድ ያለው፣

ለ./ ከታዋቂ ባንዶች ጋር በትላልቅ የሙዚቃ ዝግጅቶች ላይ በተደጋጋሚ ስራውን ያቀረበና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል

ሐ/ የተጋበዘበትን ብሔረሰብ ባህልና ቋንቋ ጠንቅቆ የሚያውቅ፣

መ/ በወቅቱ በሥራው ካሴት ያወጣ፣ ነጠላ ዜማ እና የሙዚቃ ክሊፕ የሰራው ስራ በተለያየ ሚዲ ላይ ሽፋን ያገኘ እና በህብረተሰቡም ከፍተኛ ተደማጭነት ያገኘ፣

ሠ/ በልምምድና በትርኢት ወቅት ሥራውን አክብሮ የሚገኝ፡፡

ረ/ በአንድ መድረክ ላይ በካሴት ካቀረባቸው የግል ሥራዎቹ ውስጥ ቢያንስ 3 ወጥ ሥራዎችን ማቅረብ የሚችል፡፡

ሰ/ በአጠቃላይ የኪነ - ጥበብ ሙያ ሥነ - ምግባር በማክበር ለሌሎች መሰል ሙያተኞች ተተኪ ባለሙያዎች መልካም አርአያ / **ምሣሌ** / ሊሆን የሚችል እና ከላይ የተዘረዘሩትን አራቱን እና ከዚ በላይ መመዘኛዎች ከላይ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች ማሟላቱን የየቴአትር ቤቱ የኪነ - ጥበብ አመራር ዳይሬክተር፣ስቴጅ ማናጀርና የኪነ-ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር ሲያረጋግጡና በኪነ - ጥበቡ አመራር ዳይሬክተሩ ሲፀድቅ፣ የሥራ ኮንትራት ውል እንዲፈርም በማድረግ ለድምፃዊው አርቲስት በዚሁ መመሪያ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት መድረክና የልምምድ ጊዜ የትራንስፖርት ሂሣብ ይከፈላል፡፡

12.4.2 <u>ሁለተኛ ደረጃ ተጋባዥ ድምጻዊ፣</u>

ሀ/ በመድረክ ትርዒት የማቅረብ በቂ የሙያ ልምድ ያለው፣እና ደረጃውን በጠበቀ ባለኮከብ ሆቴል ውስጥ ለሁለት ዓመት የሰራና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣

ለ/ ከታዋቂ ባንዶች ጋር በትላልቅ የሙዚቃ ዝግጅቶች ላይ ስራን ከሦስተ ጊዜ በላይ ያቀረበና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣

ሐ/ የድምፃዊነት ችሎታውን በሕዝብ ዘንድ ያስመሰከረ፣

መ/ ቢቻል በተለያዩ ቋንቋዎች መጫወት የሚችል፣

ሠ/ በአጠቃላይ የኪነ - ጥበብ ሙ.ያ ሥነ - ምግባር በማክበር ለሌሎች መሰል ሙ.ያተኞች ተተኪ ባለሙ.ያዎች መልካም አርአያ /ምሣሌ / ሊሆን የሚችል እና ከላይ ከተዘረዘሩት ሦስቱንና ከዚያ በላይ መመዘኛዎችን ማሟላቱን የየቴአትር ቤቱ የኪነ - ጥበብ አመራር ዳይሬክተር፣ ስቴጅ ማናጀርና የኪነ-ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር ሲያረጋግጡበኪነጥ - ጥበቡ አመራር ዳይሬክተሩ ሲፀድቅ ፣ የሥራ ኮንትራት ውል እንዲፈርም በማድረግ ለድምፃዊው አርቲስት በዚህ መመሪ ላይ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሰረት የመድረክና የልምምድ ጊዜ የትራንስፖርት ሂሣብ ይከፈላል፡፡

12.4.3. <u>ሶስተኛ ደረጃ ድምጻዊ፣</u>

ሀ/ በሚዘጋጅ የሙዚቃ ዝግጅቶች ወይም ሙዚቃዊ ድራማ ልዩ ባህሪ ወይም አስገዳጅነት የድምጻዊው ወጥ ሥራዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

ለ/ በተወሰነ ደረጃ በተመልካች ዘንድ ታዋቂነትና ተቀባየነት ያለው፣

ሐ/ በልምምድና በሥራ ሰዓት አስቀድሞ የሚገኝ፣

መ/ በአጠቃላይ የኪነ-ጥበብ ሙ.ያ ሥነ ምግባር በማክበር ለሌሎች መሰል ሙ.ያተኞች ተተኪ ባለሙ.ያዎች መልካም አርአያ /ምሣሌ/ ሊሆን የሚችል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች ማሟላቱን የየቴአትር ቤቱ የኪነ - ጥበብ አመራር ዳይሬክተር፣ስቴጅ ማናጀርና የኪነ-ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር ሲያረጋግጡና በኪነጥ - ጥበቡ አመራር ዳይሬክተሩ ሲፀድቅ፣ የሥራ ኮንትራት ውል እንዲፈርም በማድረግ ለድምፃዊው አርቲስት በዚህ መመሪያ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት የመድረክና የልምምድ ጊዜ የትራንስፖርት ሂሣብ ይከፈላል፡፡

12.4.4 <u>አንደኛ ደረጃ የሙዚቃ መሣሪያ ተጨዋች ተጋባዥ ሙዚቀኛ፣</u>

ሀ/ በሀገሪቱ ውስጥ ካሉ የሙዚቃ ተቋማት በሙዚቃ ትምህርት ዲግሪ እና 0 ዓመት ስራ ልምድ ዲፕሎማ እና 2 ዓመት ሰርተፊኬት እና 4 ዓመት የስራ ልምድ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣

ለ/ በሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋችነቱ /ባለሙያነቱ/ በሕብረተሰብ የታወቀ፣ እና ሙዚቃዎችን ወደ ሙዚቃ ኖታ /ስኮር/ ለውጦ ለተለያዩ ሙዚቃ መሣሪያዎች እንደመሣሪያቸው ባህሪያት ጽፎ ማቅረብ የሚችል፣

ሐ/ ነጠላ የሆኑትን ዜማ/ሜሎዲ/ ወደ ህብረ ድምፅ /ሀርሞናይዜሽን/ መለወጥ የሚችል፣

መ/ለቡድኑ ኦርኬስትራይዜሽን ሥራ ቀና ሙያዊ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችል መሆኑ የተረጋገጠለት፣

ሠ/ የተሰጠውን የሙዚቃ ሥራ ፈጥኖ የሚይዝና ለሌሎችም የሚያስዝ፡፡

ረ/ በአጠቃላይ የኪነ-ጥበብ ሙያ ሥነ ምግባር በማክበር ለሌሎች መሰል ሙያተኞች ተተኪ ባለሙያዎች መልካም አርአያ /ምሣሌ/ ሊሆን የሚችል፡፡ እና ከላይ ከተዘረዘሩት አራቱን እና ከዚያ በላይ መመዘኛዎች ማሟላቱን የየቴአትር ቤቱ የኪነ - ጥበብ አመራር ዳይሬክተር፣ስቴጅ ማናጀርና የኪነ-ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር ሲያረጋግጡና በኪነ - ጥበቡ አመራር ዳይሬክተሩ ሲፀድቅ፣ የሥራ ኮንትራት ውል እንዲፈርም በማድረግ ለድምፃዊው አርቲስት በዚህ መመሪያ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት የመድረክና የልምምድ ጊዜ የትራንስፖርት ሂሣብ ይከፈላል፡፡

12.4.5 <u>ሁለተኛ ደረጃ የሙዚቃ መሣሪያ ተጨዋች ተጋባዥ ሙዚቀኛ፣</u>

ሀ/ በሀገሪቱ ውስጥ ካሉ የሙዚቃ ተቋማት በሙዚቃ ትምህርት ዲግሪ እና 0 ዓመት ዲፕሎማና 1 ዓመት የስራ ልምድ ያለው ወይም ሰርተፊኬት እና 2 ዓመት የስራ ልምድ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣

ለ/ ወደ ሙዚቀኞች /ስኮር/ የተወጡትን ሙዚቃዎች ማንበብ የሚችል፣

ሐ/ የኦርኬስትራይዜሽን ሥራ በቂ ልምድ ያለው፣

መ/ በአጠቃላይ የኪነ-ጥበብ ሙያ ሥነ ምግባር በማክበር ለሌሎች መሰል ሙያተኞች ተተኪ ባለሙያዎች መልካም አርአያ / ምሣሌ / ሊሆን የሚችል፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች ማሟላቱን የየቴአትር ቤቱ የኪነ - ጥበብ አመራዳይሬክተር፣ስቴጅ ማናጀርና የኪነ-ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር ሲያረጋግጡና በኪነ - ጥበቡ አመራር ዳይሬክተሩ ሲፀድቅ፣ የሥራ ኮንትራት ውል እንዲፈርም በማድረግ ለድምፃዊው አርቲስት በዚህ መመሪ ላይ በተመለከተው

ሠንጠረዥ መሠረት የመድረክና የልምምድ ጊዜ የትራንስፖርት ሂሣብ ይከፈላል፡፡

12.4.6 <u>ሶስተኛ ደረጃ የሙዚቃ መሣሪያ ተጨዋች ተጋባዥ ሙዚቀኛ፤</u>

ሀ/ ለትርኢቱ በተለየ መንገድ የሙዚቃ መሣሪያውን እና ተጫዋቹን ሲፈልግ፤

ለ/ በተለያየ ምክንያት በቡድኑ ውስጥ ያሉ መሣሪያ ተጫዋች እጥረት ሲያጋጥም፤

ሐ/ በልምምድ እና በሥራ ሰዓት ቀድሞ የሚገኝ፤

መ/ በአጠቃላይ የኪነ-ጥበብ ሙያ ሥነ ምግባር በማክበር ለሌሎች መሰል ሙያተኞች ተተኪመ ባለሙያዎች መልካም አርአያ /ምሣሌ/ ሊሆን የሚችል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች ማሟላቱን የየቴአትር ቤቱ የኪነ - ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ፣ ስቴጅ ማናጀርና የኪነ-ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር ሲያረጋግጡና በኪነ - ጥበቡ አመራር ዳይሬክተሩ ሲፀድቅ ፣ የሥራ ኮንትራት ውል እንዲፈርም በማድረግ ለድምፃዊው አርቲስት በዚህ መመሪያ ላይ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት የመድረክና የልምምድ ጊዜ የትራንስፖርት ሂሣብ ይከፈላል፡፡

12.4.7. <u>አንደኛ ደረጃ ተጋባዥ የውዝዋዜ ጥበብ ባለሙያ፤</u>

ሀ/ አንድን ርዕስ ጉዳይ ይዞ ርዕሰ ጉዳዩን ገላጭ በሆነ መልኩ ራሱን ችሎታ /በሶሊስትነት/ ዝግጅት የሚያቀርብ፡፡

ለ/ በሙዚቃ ዝግጅት ወይም በሙዚቃዊ ድራማ ዝግጅት ወቅት በማይም የተሰጠውን ሀሣብ የሚገልፅ፡፡

ሐ/ በአንድ ዝግጅት ወቅት ራሱን ችሎ የተሰጠውን ርዕስ ጉዳይ ለማንኛውም የማጀቢያ ሙዚቃ ውጭ በውዝዋዜ የሚገልፅ፤

መ/ በልምምድ እና በሥራ ወቅት ሰዓቱን አክብሮ የሚገኝና ለሌሎችም አርአያ የሆነ እና ይኸው ጉዳይ በሥራ ሀላፊዎች ሲረጋገጥ የሥራ ኮንትራት ውል እንዲፈረም ተደርጐ በየትርዒቱ በመድረክ የሚከፈለውን ክፍያ እና የልምምድ ጊዜ የትራንስፖርት ክፍያ በዚህ መመሪያ ላይ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት ክፍያው ይፈፀማል፡፡

### 12.4.8. <u>ሁለተኛ ደረጃ ተጋባዥ የውዝዋዜ ጥበብ ባለሙያ፣</u>

በዚህ አንቀፅ በ"ሀ" እና በ"ለ" እና በ"መ" የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪም በአንድ ዝግጅት ወቅት ራሱን ችሎ የተሰጠውን ርዕስ ጉዳይ የማጀቢያ ሙዚቃ እየተሰጠው ርዕስ ጉዳዩን በውዝዋዜ የሚገልፅ፣

### 12.4.9. <u>ሶስተኛ ደረጃ ተጋባዥ የውዝዋዜ ጥበብ ባለሙያ፣</u>

ሀ/ መሠረታዊ የውዝዋዜ እንቅስቃሴዎችን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣

ለ/ የተለያዩ ብሔር-ብሔረሰብ ውዝዋዜ ወይም የዘመናዊ ዳንስ ስልቶችን የሚያውቅ፣

ሐ/ የተሰጠውን የውዝዋዜ ስልት ከሌሎች ቀድሞ መያዝ የሚችል እና ለሌሎች ሙያተኞችም ቀድሞ የተረዳውን የውዝዋዜ ስልት ማስያዝ የሚችል፣

መ/ በቡድን ልምምድ እና በሥራ ወቅት ሰዓቱን አክብሮ የሚገኝ እና ለሌሎች አርአያ የሆነ እና ይኸውም ጉዳይ በሥራ ሀላፊዎች ሲረጋገጥ የሥራ ኮንትራት ውል እንዲፈረም ተደርጎ በየትርኢቱ በመድረክ የሚከፈለውን ክፍያ እና የልምምድ ጊዜ የትራንስፖርት ክፍያ በዚህ መመሪያ ላይ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት ክፍያው ይፈፀማል፡፡

## 12.1 <u>የቴአትር የመድረክ ቆይታ ጊዜና የአዘቦት ቴአትር አመዳደብ፣</u>

አንድ ቴአትር ለመድረክ ከበቃበት ጊዜ ጀምሮ ለምን ያህል ጊዜያት በመድረክ ላይ እንደሚቆይ በግልጽ የተቀመጠ መመሪያ ባለመኖሩ ብዙ ተመልካች ያለውን በማስቀጠልና ተመልካች ያጣውን በማውረድ ይሰራል፣ በሌላ በኩል እያንዳንዱ ቴአትር ቤት በየዓመቱ ዕቅድ ሲያቅድ ስንት አዲስ የሰንበት ቴአትርና ስንት የአዘቦት ጊዜ ቴአትር እንደሚያቀርብ የሚያቅድ ሲሆን ከዚሁ ጋር ለሥራው የሚያስፈልገውን በጀት አብሮ ይዞ ያስፈቅዳል፡፡ በዕቅድ የሚከናወን ተግባር ደግሞ በጊዜ ገደብ ሊወሰን ስለሚገባ ይህንኑ አሰራር በመመሪያ ማስቀመጡ ተገቢ ሆኗል፡፡ በዚሁ መሠረት፡-

12.1.1 አንድ ቴአትር በድርሰት ገምጋሚ ኮሚቴ ተመርጦ ለመድረክ ከበቃ በኋላ በቂ ተመልካች ኖሮት ተመጣጣኝ ገቢ ካስገባ እስከ 2 ዓመት በመድረክ ላይ መቆየት ይችላል፡፡

12.2.2 ተመልካቹ ከቴአትር ቤቱ አዳራሽ ከ1/3ኛ በታች ከወረደና በቁጥር 12.3 የተጠቀሰውን የማይሸፍን ከሆነ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ሌላ ተተኪ ተዘጋጅቶ ከመድረክ ይወርዳል፡፡

12.2.3 ከዚህ በላይ በተ.ቁ 1 እና 2 የተገለፁት አሰራሮች እንደተጠበቁ ሆነው ቴአትሩ በቂ ተመልካች ሳይኖረው ቀርቶ ለተከታታይ 4 ሳምንታት ገቢውም የመድረክና ማስታወቂያ ወጭውን የማይሸፍን ከሆነ ከላይ የተገለፀው የጊዜ ገደብ ሳይደርስ ዝርዝር ሪፖርቱ ለፕሮሰስ ካውንስል ቀርቦ ከተገመገመ በኋላ ከመድረክ እንዲወርድ ሊወሰን ይችላል፡፡

12.2.4ቴአትሩ ተመልካች /ታዳሚ/ አለው በሚል ብቻ ረዥም ጊዜ እንዲቆይ ከተደረገ ሌሎች ባለሙያዎች የሚያቀርቧቸው ተውኔቶች እድል ስለማያገኙና አዲስ ፈጠራን ለመድረክ ለማብቃትና የፈጠራ ባለቤቶችንም ለማበረታታት ቴአትሮችን በዕቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ አንድ ቴአትር ለመድረክ እንደበቃ ወዲያውኑ ሌላ ጽሑፈ ተውኔት ተቀብሎ መገምገምና ለቀጣይ ፕሮግራም ማዘጋጀት የቴአትር ቤቱ ኃላፊነት ይሆናል፡፡

12.2.5 በቴአትር ቤቱ መድረክ ከላይ በተ.ቁ 1 እና 2 መሠረት ሲታይ ቆይቶ ከመደበኛ ፕሮግራም የወጣ ቴአትር በአዘቦት ፕሮግራም ውስጥ ገብቶ እንዲታይ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በተራ ቅደም ተከተላቸው መሠረት ተመዝግበው በፕሮሰስ ካውንስል እየተወሰነ እንደ ተመልካቹ ብዛትና ገቢ ለአንድ ዓመት መታየት ይችላል፡፡

12.2.6 ይህ የቴአትር የመድረክ የቆይታ ጊዜ ከቴአትር ቤቶች መድረክ ተከራይተው ለሚሰሩ ድርጅቶችም ይሰራል፡፡ ያም ሆኖ ድርጅቶቹን ለማበረታታትና የተመልካቹን ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት የቆይታ ጊዜው 6 ወራት ሊራዘም ይችላል፡፡

12.2.7 ቴአትር ቤቱ 70% መድረኮችን በራሱ ፕሮዳክሽን መሸፈን ይገባዋል፡፡ ለውጭ ኢንተርፕራይዞች ደግሞ እስከ 30% ሊያከራይ ይችላል፡፡

## 12.3 የኪነ-ጥበብ አገልግሎት ጥያቄ ሲቀርብ ስለሚስተናገድበት አሰራር፣

መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶችና ተቋማት ከቴአትር ቤቶች ለሚፈልጓቸው የኪነ-ጥበብ ውጤቶችና የአዳራሽ ኪራይ አገልግሎት ከቴአትር ቤቶች መድረክ ውጭ ለሚሰጡ የኪነ-ጥበብ ውጤቶች አገልግሎት ለመስጠትና ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት አገልግሎቶች እየተሰጡ ቢሆንም አሰራሩ ወጥ ያልሆነና ለሁሉም ቴአትር ቤቶች ፍትሃዊ ስርጭትን መሠረት ያላደረገ ነው፡፡ የውጭ ሥራ የሚከናወነው ተመሳሳይ ሙያ ባላቸው የኪነጥበብ ባለሙያዎች በመሆኑ የሚቀርቡት ጥያቄዎች በአግባቡ ሊስተናገዱ ይገባል ከዚሁ መሠረተ ሀሣብ በመነሳት፣

12.3.1 ማናቸውም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶችና ተቋማት ቴአትርም ሆነ ሙዚቃ እንዲቀርብላቸው ሲጠይቁ ጥያቄያቸውን ለቴአትር ቤቶች ይቀርቧሉ፡፡ እንዲሁም በቢሮው በኩል የሚያቀርቡ ካሉ ቴአትር ቤቶች ተቀብለው ያስተናግዳሉ፡፡

12.3.2 ቴአትር ቤቱ ጥያቄው እንደደረሰው ምላሽ ይሰጣል፡፡ ከአሠሪው አካል ጋር ስምምነት ከተደረሰ በሚፈፀመው ውል መሠረት ዝግጅት ተደርጎ ትርዒቱ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

12.3.3 በውል የተወሰነውን ክፍያ በደረሰኝ ገቢ ካስደረገ በኋላ ዝግጅቱን አጠናቆ ትርዒቱን ለጠያቂው ክፍያ ያቀርባል፡፡

12.3.4. ለጠያቂው ክፍል ትርዒት የሚያቀርበው ቡድን የባለሙያዎች ስብጥር የሚወስነው በሥራ ክፍሉ የኪነ-ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር ሲሆን በኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ይፀድቃል፡፡

12.3.5. ዝግጅቱን ለማቅረብ ውል ከተፈረመ በኋላ በሥራ ላይ ጉድለት ቢገኝ ወይም በጠያቂው ክፍል በኩል ቅሬታ ቢቀርብ ኃላፊነቱ የኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ይሆናል፡፡

12.3.6. ውል ከተፈረመ በኋላ በጠያቂው ክፍል ጉድለት ምክንያት ትርኢቱ ባይቀርብ ለባለሙያዎችና ለመንግስት የተፈፀመው ክፍያ አይመለስም፡፡

## ክፍል ስድስት

## 13. የቴአትር ቤቶች አዳራሽ አገልግሎት አሰጣጥ፣ ስለጽዳትና የላብ ማካካሻ ክፍያ እና ስለ የትርዒት መግቢያ ዋጋ ተመን

### 13.1. የቴአትር ቤቶች አዳራሽ አግልግሎት አሰጣጥ

13.1.1ቴአትር ቤቶች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ደንበኞች የሚስተናገዱበት ተቋማት በመሆናቸው ጥንቃቄ የተሞላበት የግቢና የንብረት ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፣ በሥራቸው ልዩ ባህሪ የተነሳ ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ እንዲሰሩ ስለሚገደዱ ለቴአትር ቤቶች ንብረቶች ብቻ ሳይሆን ለደንበኞችም ሆነ ደንበኞች ወደ ቴአትር ቤቱ ይዘዋቸው ለሚመጡት ንብረቶች የጥበቃ ዋስትና ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በዚህም መሠረት ከ3[ኛ] ወገን የሚቀርበውን ጥያቄ ለማስተግናድ እንዲቻል፡-

13.1.2 የግል የኪነ-ጥበብ ተቋማት ማለትም የቴአትር፣ የሙዚቃ፣ የፊልም፣ የስዕልና ቅርፃ ቅርፅ፣ የሰርከስ፣ የኮሜዲ፣ የአክሮባትና የማርሻል አርት ወዘተ... ኢንተርፕራይዞች፣ፕሮሞሽኖች፣ጋለሪና ስቱዲዮዎች ብሎም የፕሮዳክሽን ባለሙያዎች ሥራዎቻቸውን በቴአትር ቤት ማቅረብ ሲፈልጉ እንደ የቴአትር ቤቶቹ ትርዒት የማቅረብና በአዳራሹ የመገልገል ጥያቄ ቅደም ተከተል አመዘጋገብ መሠረት ለማስተናገድ ማሟላት የሚገባው፡-

ሀ/ ከባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተሰጠ የማጣያ/ማሠራጫ የሙያ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ፣
ለ/ የኪነ-ጥበብ ዝግጅቱን ዓይነት መግለጽ ይጠበቅበታል፣
ሐ/ ህጋዊ ቀረጥ የተከፈለበት የመግቢያ ትኬት ማቅረብ፣
መ/ ትርዒቱ እንዲታይ የሚፈልግበትን ቀንና ሰዓት መግለጽ፣
ሠ/ ትርዒቱ የሚፈጀውን ሰዓት መግለጽ አለበት፣
ረ/ የአገልግሎት ፈላጊው ድርጅት ስምና አድራሻ መግለጽ አለበት፣
ሰ/ ለአገልግሎቱ የሚፈለግ አጋዥ መሣሪያ የሚያስፈልግ ከሆነ መግለጽ አለበት፣
ሸ/ ለአገልግሎቱ የሚፈለግ ተጨማሪ መስተንግዶ ካለ ወዘተ... የሚገልጽ ዝርዝር መረጃ የያዘ ደብዳቤ ለሚፈልጉት ተቋም ወይም ቴአትር ቤት ማቅረብ አለባቸው፡፡

13.1.3 ለተቋሙ የሠራተኛ መረጃና ሪከርድ ኦፊሰር የአገልግሎት ጥያቄው ደብዳቤ የደረሰበት ቀንና ፣ሰዓት ተመዝግቦ ፣ ከአገልግሎት ጥያቄ ደብዳቤ ጋር አባሪ የተደረጉ ከላይ ከንዑስ ቁጥር ከሀ እስከ ሸ ድረስ የተዘረዘሩትን መረጃዎች በመዝገቡ ላይ በማስፈር የአዳራሽ አገልግሎት ለማግኘት ወረፋቸውን ይጠብቃሉ፡፡

13.2 ስለ ጽዳትና የላብ ማካካሻ ክፍያ አፈፃፀም፣

የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች በቴአትር ቤት መድረክም ሆነ ከቴአትር ቤት ውጭ ሲሰሩ የሚወጣቸውን ላብ ለመተካት ክፍያ እንደሚያስፈልጋቸው በኪነ-ጥበብ ፈጠራ ሥራዎች የባለሙያዎች ማበረታቻና የአገልግሎት ክፍያው በዚህ መመሪያ ላይ በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት ክፍያ ይፈፀማል፡፡

13.2.1 ከላይ የተገለፁት ክፍያዎች አገልግሎት ጠያቂው ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ከቴአትር ቤቱ ጋር የቴአትር ቤቱን መደበኛ ክፍያ ሲዋዋል እነዚህንም ለመፈፀም ፈቃደኝነቱን ተጠይቆ ከተስማማ ክፍያዎች በውሉ ውስጥ ተካተው በመደበኛ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ሳይቆረጥባቸው ክፍያውን በወሰዱት ሠራተኞች ፊርማ ሂሳቡ ይወራረዳል፡፡

13.2.2. በቴአትር ቤቱ አዳራሽ በኪራይም ሆነ በሌላ ሁኔታ የትርዒትም ሆነ የስብሰባ አገልግሎት ሲሰጥ ለሚሳተፍ የአዳራሽ አስተባባሪ፣ አስተናጋጅ፣ ጥበቃ፣ የጽዳት ሠራተኞች፣ ትኬት ቆራጮች፣ የቴክኒክ ባለሙያዎች ፣ስቴጅ ማናጀር ከሌለም ከኘሮሰስ ካውንስል የሚወከል ከአገልግሎት ጠያቂው የሚከፈል ለእያንዳንዱ ሠራተኛ የላብ ማካካሻ እና የንፅህና ብር 50 ይከፈላል፡፡ ይህም አከፋፈል እስከ 16 የሚደርሱ ፈጻሚ ሠራተኞች ይመደባሉ፡፡ ከ16 የሰው ኃይል በላይ መመደብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ግን ከአገልግሎት ጠያቂው በሚቀርበው ጥያቄ መሠረት ይመደባል፡፡ ሂሳቡ የሚወራረደውም በውሉ ላይ በተመለከተው መሠረት በሠራተኞች ፊርማ ይሆናል፡፡

## 13.3 የቴአትር ቤቶች የትርዒት መግቢያ ዋጋ ተመን፣

ለፈጠራ ውጤቶችና ባለሙያዎች የሚከፈለው ክፍያ ከወቅቱ ተጨባጭ የገበያ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ስላልሆነና በዘላቂነት ሙያውንና ባለሙያውን የሚያበረታታ ባለመሆኑ እስከ አሁን የሚሰራው ቀደም ሲል በወጣው መመሪያ ሲሆን አሁን ከጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ለእያንዳብዱ ትርዒት የሚከተለው የመግቢያ ዋጋ ተመን ተወስኗል፡፡

*የቴአትር ቤቶች የትርዒት ማባያ ዋጋ ተመን ሠንጠረዥ*

| ተ.ቁ | የክፍያው አርዕስት | የክፍያ መጠን በብር |
|---|---|---|
| 1 | የመደበኛ ቴአትር ቤቶች | |
| 1.1 | የቴአትር መግቢያ | 30.00 |
| 1.2 | የፊልም መግቢያ | 25.00 |
| 1.3 | የሙዚቃ መግቢያ | 30.00 |
| 1.4 | የሙዚቃዊ ድራማ መግቢያ | 30.00 |
| 2 | የህፃናትና ወጣቶች ቴአትር /ለአዋቂ/ | |
| 2.1 | የቴአትር መግቢያ | 10.00 |
| 2.2 | የፊልም መግቢያ | 10.00 |
| 2.3 | የሙዚቃ መግቢያ | 10.00 |
| 2.4 | የሙዚቃዊ ድራማ መግቢያ | 10.00 |
| 3 | የህፃናትና ወጣቶች ቴአትር /ለህፃናት/ | |
| 3.1 | የቴአትር መግቢያ | 7.00 |
| 3.2 | የፊልም መግቢያ | 7.00 |
| 3.3 | የሙዚቃ መግቢያ | 7.00 |
| 3.4 | የሙዚቃዊ ድራማ መግቢያ | 7.00 |

14. ቴአትር ቤቶች የግቢና የንብረት ጥበቃ አሰራር

14.1 ለሥራው የተመደቡ የጥበቃ ሠራተኞች ጥንቃቄ በተሞላበት ኃላፊነት ተረኛ ሆነው ሲመደቡ ግቢውን፣ የቴአትር ቤቱንና የደንበኞችን ንብረት በተገቢው ጥንቃቄ መጠበቅና የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው፡፡

14.2 በመደበኛና በአዘቦት የትርዒት ኘሮግራም ካበቃ እና እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት የሚጠናቀቅ ከሆነ ፕሮግራሙ ከተጠናቀቀ ከ30 ደቂቃ በኋላ ተገልጋዩንም ሆነ የተገልጋዩችን ንብረቶች በማስወጣት በግቢው ላይ ቁጥጥር በማድረግ ግቢውን መዝጋት አለባቸው፡፡

14.3 ማንኛውም ቴአትር ቤት ትርዒት ከሥራ ሰዓት ውጭ የሚቀርብ ሆኖ እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት የሚቆይ ካልሆነ በስተቀር የማንንም ንብረት/ ተሽከርካሪ/ ተረክቦ ማሳደር ወይም ማስቀመጥ ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ተቋማት የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ ተቸግረው በደብዳቤ ሲጠይቁና በህጋዊ መንገድ ሲፈቀድላቸው ማሳደር ይችላሉ፡፡ ከዚህ ውጭ ፈጽሞ የተገኘ ኃላፊም ሆነ የጥበቃ ሠራተኛ በከባድ የዲስኘሊን ግድፈት የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ ለሚደርስ ጉዳትና አደጋ በግሉ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

14.4 በመንግስት ተቋም ውስጥ ማናቸውም ዓይነት ገጽታውን የሚያበላሽ ለግል ወይም ለቡድን ጥቅም ሲባል ከሌሎች አካላት ጋር በመመሳጠር በግቢው ውስጥ የሚፈፀም ተግባር በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ ማናቸውም ከተቋሙ ዓላማ ውጭ የሆነ ተግባር ተፈጽሞ ከተገኘ የተቋሙ ኃላፊ እና የጥበቃ ሠራተኞች በዲሲፒሊን ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሰባት

## 15. የኪነ-ጥበብ የፈጠራ ሥራዎች፣ የባለሙያዎች ማበረታቻና የአገልግሎት ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ

### 15.1 የቲያትር ክፍያን በተመለከተ፡-

የቲያትር ድርሰት፣ ዝግጅት፣ትወና፣የቴክኒክ ባለሙያ እና ስቴጅ ማናጀር የክፍያ ተመኑ ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት ሆኖ የአከፋፈሉ አፈጻጸም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ቲያትር ቤቶች ከደራሲዎች ጋር በሚፈፅሙት የውል ስምምነት ቲያትር ለማዘጋጀት የመድረክ ግንባታ፣ የአልባሳት ፣ቁሳቁስ፣ የገፅ ቅብ፣ የሜካፕ፣ የፖስተር፣ የተለያዩ ማስታወቂያዎች እና ሌሎች አስፈላጊ ወጪዎች በሙሉ የፕሮዲውሰር /የቲያትር ቤቱ/ ወጪዎች ይሆናሉ፡፡ስለሆነም ቲያትሩ ለሕዝብ ቀርቦ መታየት ከጀመረ ከወር በኃላ የፈጠራ ክፍያ ጥያቄ በአዘጋጁ ይቀርባል፡፡ በስቴጅ ማናጀሩ ተረጋግጦ ለኪነ- ጥበብ አመራር ዳይሬክተሩ ለውሣኔ ይቀርባል፡፡ ዳይሬክሩም ለፋይናንስ ከመራ በኃላ ከዚህ ጋር በተያያዘው ውል መሠረት ሂሣቡ ተሠርቶ ሲቀርብ ክፍያው ይፈፀማል፡፡

የኪነ ጥበብ የፈጠራ ስራዎች፣የባላሙያዎች ማበረታቻና አገልግሎት ክፍያ ሠንጠረዥ

ቴአትርን በተመለከተ

| ተ.ቁ | የክፍያው አርዕስት | የክፍያ መጠን በፐርሰንት |
|---|---|---|
| 1 | **ወጥ/ኦርጅናል/ ድርሰት/ ከዕለት ገቢ** | |
| | ለቴአትር ቤቱ | 45 |
| | ለደራሲ | 30 |
| | ለአዘጋጅ | 10 |
| | ለተዋንያን | 10 |

| ተ.ቁ | የክፍያው አርዕስት | የክፍያ መጠን በፐርሰንት |
|---|---|---|
| | ለቴክኒክ ባለሙያዎች | 3 |
| | ለእስቴጅ ማናጀር | 2 |
| 2 | **ለውርስ ትርጉም/ድርሰት/ ከዕለት ገቢ** | |
| | ለቴአትር ቤቱ | 50 |
| | ለአዛማጅ ተርጓሚ | 25 |
| | ለአዘጋጅ | 10 |
| | ለተዋንያን | 10 |
| | ለቴክኒክ ባለሙያዎች | 3 |
| | ለእስቴጅ ማናጀር | 2 |
| 3 | **ለቀጥታ ትርጉም/ድርሰት/ ከዕለት ገቢ** | |
| | ለቴአትር ቤቱ | 55 |
| | ለተርጓሚ | 20 |
| | ለአዘጋጅ | 10 |
| | ለተዋንያን | 10 |
| | ለቴክኒክ ባለሙያዎች | 3 |
| | ለእስቴጅ ማናጀር | 2 |

## 15.2 የተጋባዥ ተዋንያን የመድረክ ክፍያ፣-

የክፍያ ተመኑ ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት ሆኖ የደረጃ አወሳሰኑም በዚህ መመሪያ መሠረት ሆኖ የክፍያው አፈጻጸሙም ቲያትሩ ለህዝብ ከቀረበ በኃላ በየወሩ ከአዘጋጅ ጥያቄ ሲቀርብ በስቴጅ ማናጀሩ ተረጋግጦ ዳይሬክሩም ለፋይናንስ ከመራ በኃላ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ውል መሠረት ሂሣቡ ተሠርቶ ሲቀርብ ክፍያው ይፈፀማል፡

__ለተጋባዥ ተዋንያን የመድረክ ክፍያ ሠንጠረዥ__

| ተ.ቁ | ባለሙያ | የክፍያ ተመን በብር |
|---|---|---|
| 1 | 1ኛ ደረጃ ተዋናይ | 500.00 |
| 2 | 2ኛ ደረጃ ተዋናይ | 300.00 |
| 3 | 3ኛ ደረጃ | 200.0 |
| 4 | ለተጋባዥ ተዋናይ የልምምድ እና የትራንስፖርት በወር | 300.00 |

## 15.3 የኪነጥበብ የፈጠራ ሥራዎች የባለሙያዎች ማበረታቻና የአገልግሎት ክፍያ ሠንጠረዥ ሙዚቃን በተመለከተ በተናጠል የሚቀርቡ የፈጠራ ሥራዎች ክፍያ፡-

በተናጠል የሚቀርቡ የፈጠራ ሥራዎች ክፍያ ተመኑ ከዚህ በታች በተቀመጠው ሠንጠረዥ ሆኖ የክፍያ አፈጻጸሙም ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ የሙዚቃ ትርኢቱ ለሕዝብ ከቀረበ በኃላ የክፍያ ጥያቄው በዘርፉ በተመደበ የኪነጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር አማካኝነት ሲቀርብ በስቴጅ ማናጀሩ ተረጋግጦ ለኪነ-ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ለውሣኔ ይቀርባል፡፡ ዳይሬክተሩም ለፋይናንስ ከመራ በኃላ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ውል መሠረት ሂሣቡ ተሠርቶ ሲቀርብ  ክፍያው ይፈፀማል፡፡

__*የኪነ ጥበብ የፈጠራ ስራዎች፣የባለሞያዎች ማበረታቻና አገልግሎት ክፍያ ሠንጠረዥ*__

__*ሙዚቃን በተመለከተ በተናጠል የሚቀርብ የፈጠራ ስራዎች ክፍያ*__

| ተ.ቁ | የክፍያው አርዕስት | የክፍያ ማጠን በብር |
|---|---|---|
| 1 | ለ 1ኛ ደረጃ ዜማ | 1000.00 |

| ተ.ቁ | የክፍያው አርዕስት | የክፍያ ማጠን<br>በብር |
|---|---|---|
| 2 | ለ 2ኛ ደረጃ ዜማ | 800.00 |
| 3 | ለ 3ኛ ደረጃ ዜማ | 600.00 |
| 4 | ለ 1ኛ ደረጃ ግጥም | 1000.00 |
| 5 | ለ 2ኛ ደረጃ ግጥም | 800.00 |
| 6 | ለ 3ኛ ደረጃ ግጥም | 600.00 |
| 7 | ለ 1ኛ ደረጃ ሚዜቃ ቅንብር | 1000.00 |
| 8 | ለ 2ኛ ደረጃ ሚዜቃ ቅንብር | 800.00 |
| 9 | ለ 3ኛ ደረጃ ሚዜቃ ቅንብር | 600.00 |
| 10 | ለ 1ኛ ደረጃ ውዝዋዜ/ዳንስ/ | 1000.00 |
| 11 | ለ 2ኛ ደረጃ ውዝዋዜ/ዳንስ/ | 800.00 |
| 12 | ለ 3ኛ ደረጃ ውዝዋዜ/ዳንስ/ | 600.00 |

ቴአትር ቤቶች በየጊዜው የሚወጡትን አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎች ግጥም፣ ሙዚቃ፣ ቅንብር፣ ኪሮግራፊ ለመድረክ ከበቁበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለት ዓመት ከተጠቀሙበት በኋላ በድጋሚ ለቀጣይ ሁለት ዓመት መጠቀም ከፈለጉ 50% ክፍያ መፈፀም ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 15.4 በቴአትር ቤቶች በየወቅቱ የሚዘጋጅ የፈጠራ ሥራዎች ላይ የሚሳተፉ አርቲስቶች ለማበረታቻ የሚከፈል ክፍያ፣

የዚህ ክፍያ ተመን ከዚህ በታች በተቀመጠው ሠንጠረዥ ላይ የተመለከተው ሆኖ የክፍያ አፈጻጸሙም የደራሲዎች ክፍያ እንደተፈፀመ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ተሣታፊዎች ዝርዝር በዘርፉ በተመደቡ የኪነ-ጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰሮች ሲቀርብ በስቴጅ ማናጀሩ ተረጋግጦ ለኪነ -ጥበብ አመራር ዳይሬክተር ለውሣኔ

**ይቀርባል፡፡ዳይሬክተሩም ለፋይናንስ ከመራ በኃላ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ውል መሠረት ሂሣቡ ተሠርቶ** ክፍያው ይፈፀማል፡፡

*__በቴአትር ቤቶች በየወቅቱ የሚጋጅ የፈጠራ ሥራዎች ላይ የሚተፉ አርቲስቶች ለማበረታቻ የሚከፈል ክፍያ ተመን__*

| *ተ.ቁ* | *የክፍያው አርዕስት* | *የክፍያ ማጠን በፐርሰንት* |
|---|---|---|
| 1 | ቀጥተኛ ተሳታፊዎች | |
| | ማዚቀኞች፣ደምጻዊያን፣ተወዛዋገቾ እና አስተባባሪዎች ከደራሲው | 15 |
| | ማዚቀኞች፣ደምጻዊያን፣ተወዛዋገቾ እና አስተባባሪዎች ከቴያቴር ቤቱ | 10 |
| 2 | ቀጥተኛ ያልሆኑ ተሳታፊዎች | |
| | ለቴክኒክ ባለሞያዎች ከደራሲው | 5 |
| | ለቴክኒክ ባለሞያዎች ከቴያትር ቤቱ | 3 |

## 15.5 የተጋባዥ የሙዚቃ ባለሙያዎች የመድረክ ክፍያ፣

የክፍያ ተመኑ ከዚህ በታች በተቀመጠው ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፡፡ የክፍያ አፈጻጸሙም በዘርፉ የተመደበው የኪነጥበብ ልማት ሲኒየር ኦፊሰር የክፍያ ጥያቄ ሲያቀርብ በስቴጅ ማናጀሩ ተረጋግጦ ለኪነጥበብ አመራር ዳይሬክተር ለውሣኔ ያቀርባል፡፡ዳሬይክተሩም ለፋይናንስ ከመራ በኃላ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ተደርጎ በተያያዘው ውል መሠረት ሂሣቡ ተሠርቶ ሲቀርብ ክፍያው ይፈፀማል፡፡

*ለተጋባዥ የሙዚቃ ባለሙያዎች የመድረክ ክፍያ ተመን*

| ተ.ቁ | የክፍያው አርዕስት | የክፍያ ማጠን<br><br>በብር |
